ክፍል አንድ

የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት

- ሐዲስ ኪዳን ምንድን ነው?

ሐዲስ ኪዳን የማይሻር ዘለዓለማዊ አዲስ ውል፣ቃልኪዳን፣መሐላ፣ስምምነት ማለት ነው።

- የሐዲስ ኪዳን ክፍሎች

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በአምስት እንከፋፍላቸዋለን እነርሱም

- የወንጌል
- የታሪክ
- የመልዕክታት
- የትምህርት
- የሥርዓትና
- የትንቢት ክፍሎች ናቸው።

1 የምሥራች (ወንጌል) ክፍል

ወንጌል የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙም የምስራች ማለት ነው።ወልድ በሥጋ ተገልፆ ያደረገውን የማዳን ጉዞ ለሰዎች የሰጠውን ከኃጥያትና ከዲያብሎስ ባርነት ነፃ መውጣት ስለሚገልፅ ወንጌል የምስራች ተብሏል።፬ሐፊያኑም ወንጌላውያን ሲባሉ ማቴዎስና ዮሐንስ ከሐዋርያት ማርቆስና ሉቃስ ከአርድእት ወገን ናቸው።ወንጌላውያን ከፍ ብለው አምስት ዝቅ ብለው ሦስት ያልሆኑበት/ አራት ብቻ የሆኑበት ምክንያት

- የጌታችን ዙፋን ከሚሸከሙት 4 ቱ እንስሳት ምሳሌ ወንጌላዊያኑም አራት ሆነዋል ራእይ **4÷7 ፤6÷2** የሰው፣የንስር፣የአንበሳ እና የላም ናቸው።
- በአራቱ አፍላጋት(ወንዞች)ይመሰላሉ።እነዚህም ከገነት ከአንድ እጸ ሕይወት ስር መንጭተው ይህን ዓለም ዙረው አጠጥተው እጽዋትን ከመድረቅ ወደ ልምላሜ፣ከልምላሜውም ጽጌ(አበባ) ከጽጌ ወደ ፍሬ ያደርሳሉ።ልክ እንደዚሁ አራቱ ወንጌላዊትም ወንጌልን ከአንድ ጌታ ተምረው ይህን ዓለም ዙረው አስተምረው ምዕመናንን በኃጥያት ከመድረቅ ወደ ልምላሜ ንሰሐ፣ከልምላሜ ንሰሐ ወደ ጽጌ ትሩፋት ወደ ፍሬ ክብር ያደርሳሉና።
- በአራቱ አዋክብት ይመሰላሉ እነዚህም አራቱ ክዋክብት ህልመልሚሌክ ምልክኤል ምኤል ንርኤል በመባል ይጠራሉ።
- በአራቱ ወቅቶች ይመሰላሉ፡እነዚህም ጸደይ ክረምት መጸው ሐጋይ(በጋ) ተብለው ይጠራሉ።

ጸደይ፡- የዘር ወቅት ነው ማቴዎስ በዚህ ይመሰላል ምክንያቱም የዘር ምሳሌን ከሁሉ ይልቅ አምልቶ አስፍቶ ጽፏልና

ክረምት፡-የውሀ ወር ነው ማርቆስ በዚህ ይመሰላል ምክንያቱም ወንጌሉን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት ይጀምራልና

መጸው፡- የነፋስ ወር ነው ሉቃስ በዚህ ይመሰላል ምክንያቱም በነፋስ አምሳል መንፈስ ቅዱስ እንደሚሰጥ ተናግሯል እንዲሁም እመቤታችን «መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል የልዑል ኃይልም ይፀልልሻል» እያለ ጽፏልና

ሐጋይ(በጋ)፡-ወርሀ እሳት ነው ዮሐንስ በዚህ ይመሰላል ምክንያቱም እርጥበት የሌለበት ደረቅ ወር ነው መስተጻረር መስተቃረን የሌለበት ደረቅ ቃል በመጀመሪ ቃል ነበር...እያለ ጽፏልና

- እንዲሁም አራቱ ወንጌላውያን ሁለቱ ከሐዋርያት ሁለቱ ደግሞ ከአርእድት ወገን ናቸው።

ለምን ሐዋርያት ብቻ ያልጻፉት?

- ✓ ጌታ ወንጌሉን ሐዋርያት ጨርሰው እንዲድፋት ቢያደርግ ኖሮ አርድእት ለማስተማር ሲወጡ እናንተንማ ማን ይሰማችኃል የውጭ ሰው ናችሁ የውጭ ሰዎችማ ብትሆቱ ወንጌልን በዳፋችሁ ነበር ብለው አይሁድ ትምህርታቸውን ከከመቀበል ወደኃላ ባሉ ነበር።
- ✓ የአርድእት ክብር በአይሁድም ዘንድ ሆነ በክርስትያኖች ባልታወቀ ነበር።አሁን ግን አርድት በጌታ ዘንድ የከበሩ መሆናቸውን ወንጌልን ለማዳፍ ታወቀ።

ለምን አርድእት ብቻ ያልጻፉት?

- ✓ ስለ ወንጌል ክብር

በአጠቃላይ ወንጌል በአርድእት ብቻ ተጽፎ ቢሆን ኖሮ ይህችማ ተርታ ሕግ ናት ደጊቱማ ሕግ ምሥጢረ ታምራትን በቤተ ኢያኢሮስ ምሥጢረ መንግስትን በደብረ ታቦር ምሥጢረ ምጽአትን በደብረዘይት ምሥጢረ ፀሎትን በጌቴ ሰማኒ ባዩ አዕማደ ምድር በተባሉ በልበ ሐዋርያት ቀርታለች በማለት አይሁዳ ደገኛይቱን ሕገ ወንጌል ከመቀበል በተከላከሉ ነበር።

1.1 የቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል

በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ትውፊት መሠረት የቅዱስ ማቴዎስ አባቱ ዲቁ እናቱ ክሩትያስ ይባላሉ።በማርቆስ ወንጌል ላይ የአባቱ ስም እልፍዮስ ተብሎ ተጠርቷል።ይህም የዲቁ ሌላ ስሙ ነው/ማር÷14/ የመጀመሪያ ስሙ ሌዊ ስሆን ማቴዎስ የሚለውን ስም ያወጣላት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።ትርጉሙም የተመረጠ ማለት ነው።

ማቴዎስ የቀድሞ ሥራው ቀራጭነት(ግብር ሰብሳቢ) ሲሆን ይሠራበት የነበረው ቦታ በገሊላ ባሕር አጠገብ በምትገኘው ደማቁ ቅፍረናሆም ከተማ ነበር።ከቅፍረናሆም ገብያ ወደ ገሊላ ባሕር ወደብ በሚወስደው ዐብይ መንገድ ዳር ሱቅ ከፍቶ ነጋዴዎችን ቀረጥ ያስከፍል ነበር።ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚያ ሲያስተምር ወደ ሚቀርጥበት ቦታ ጠጋ ብሎ«ተከተለኝ»አለው።ቅዱስ ማቴዎስ እርሱ የሚሠራውን አስቦ ድሆችን በነዳ የሚያበላ ድውያንን በነዳ የሚፈውስ ሲያገኝ ተገርሞ ሥራውን እርግፍ አድርጎ ትቶ ተከተለው።አባቶቻችን ቅዱስ ማቴዎስን «የቁም ተስካሩን አውጥቶ ጌታን የተከተለ ሐዋርያ» ይሉታል።ለሐዋርያነት በተመረጠ ጊዜ በቤቱ ደግሶ ጌታን ጋብዞ ድሆችን መጽውቶ ተከትሎታልና።/ማቴ **9÷10-13/**

ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በፍልስጤም፣በፋርስ፣በባቢሎን፣በኢትዮጵያ ወ.ዘ.ተ እንደሰበከ ይናገራል።ዩሐንስ አፈወርቅ በበዓለ ሃምሳ ድርሳኑ እንደገለጠው በቤተክርስቲያን ታሪክ በኢትዮጵያ መጀመሪያ ወንጌልን የሰበኩት በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ሄድው በነበሩበት ወቅት በሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት ካመኑት 3 ሺ ምመናን መካከል የነበሩት ኢትዮጲያውያን ሲሆኑም ቀጥሎም ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ነው።የቅዱስ ማቴዎስ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ከእነዚህ በኃላ ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በኢትዮጵያ ወንጌልን እንዳስተማረ የቤተክርስትያን ታሪክ ፀሐፊ ሩፊኖስ አረጋግጧል።የአገራችን ሊቃውንትም ያስተማረው በትግራይ በስተ ምእራብ በአድዋ አውራጃ ልዩ ስሙ ናዕዴር በተባለ ቦታ መሆኑን ይናገራሉ።አንድ በአረበኛ የተፃፈ ስንክሳር ደግሞ በ ገፅ 76 ላይ ወንጌላዊው ማቴዎስ በትግራይ እንደሰበከ ይገልፃል።ሊቃውንተ ቤ/ክ ለዚህ የሚያቀርቡት ማስረጃ የራሱን ወንጌል ነው።ቅዱስ ማቴዎስ ከሌሎች ወንጌላውያን ተለይቶ የሰብዓ ሰገልን (የጥበብ ሰዎችን)ታሪክ የፃፈው በነዚህ አገሮች በማስተማሩ ነው ይላሉ።

«የተርሴስና የደሴቶች ነገስታት ስጦታን ያመጣሉ፤የዓረብና የሳባ ነገስታት እጅ መንሻን ያቀርባሉ» መዝ **71 (72) ÷40** ባለው የቅዱስ ዳዊት መዝሙር የተርሴስና የደሴቶች የተባሉት ፋርስና ባቢሎን ሲሆን የዓረብና የሳባ የተባሉት ደግሞ የመንና ኢትዮጵያ ናቸው።

ከጥንት ዘመን ጀምሮ ከኢትዮጵያ በስተምሰራቅ ያለው ሀገር እስከ ሕንድ ድረስ ያለው ምስራቅ እየተባለ ይጠራል።ማቴዎስ በወንጌሉ «ከምስራቅ የመጡ» ያለው በዚህ መሰረት ነው።ገድለ ሐዋርያት ቅዱስ ማቴዎስ በግሪክ(አጽሎን የተባለ ጣዖት ይመለክበት በነበረ ቦታ)እንዳስተማረ ይናገራል።በመጨረሻ ግን በፍልስጥኤም ሲያስተምር የአይሁድና የአረማውያንንም ትምህርት በመቃወሙ ድውያንን ሲፈወስ አጋንንት ሲያወጣ በማየታቸው የሀገሩ ሰዎች ወደ እስር ቤት ጣሉት።

በእስር ላለ ያጋጠመውን እስረኛ ተአምር ነግሮ ከጌታው ቁጣ በማዳኑ ወሬው በሀገሩ ሁላ በማቴዎስ ላይ በመዳረሱ ይህንን የሠሙት መኳንንትም ማቴዎስን ለንጉሡ ከስሱት።ንጉሡም በመኳንንቱ ተመርቶ በማቴዎስ ላይ ሞትን ፈረደበት።ጥቅምት 12 ቀን አንገቱን ተሰይፎ አረፈ።

የቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል በምራፎች ብዛት የመጀመሪያውን ወንጌል በመሆን 28 ምዕራፎች ይዟል።የተፃፈው ከቅዱስ ማርቆስ ወንጌል ቀጥሎ በ 58 ዓ.ም አካባቢ ነው።የጌታችን ትምህርት በሰፊው በማቅረብ ቀዳሚውን ስፍራ ይዟል።በዚህም አቀራረቡ ከዮሐንስ ወንጌል ጋር ሲዛመድ ከሉቃስና ከማርቆስ ወንጌል ይለያል።ወንጌሉን የፃፈው ለአይሁድ በመሆኑ ከ 150 በላይ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን አቅርቧል።በነዚህም የተናሳ ብሉይ ኪዳንን አብዝቶ በመጥቀስ ከሌሎች ወንጌሎች ይበልጣል።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቀድሞ በነብያት የተነገረለት መሲሕ መሆኑን ለማስረገጥ ሲል አንድን ታሪክ ከዳፉ በኋላ በነብይ የተጻፈው ብሎ ይመሰክራል።ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ ትውፊትን በብዛት የተጠቀመ ሐዋርያ ነው። ማቴዎስ ወንጌልን ስላፃፈበት ቋንቋ ሦስት ዓይነት ሐሳብ ቀርቧል።

በዕብራይስጥ፡-የቤተክርስቲኒያችንን ሊቃውንት ጨምሮ ብዙ ምሁራን የተስማሙት ቅዱስ ማቴዮስ ወንጌሉን በዕብራይስጥ ቋንቋ ጻፈው በሚለው ሐሳብ ነው። ነገር ግን እስካሁን ድረስ የዕብራይስጡ ዋና ቅጂ አልተገኘም።

በአረማይክ፤-ፓፒየስ የተባለው አባት በ 2 ኛው ክ/ዘመን እንደገለጠው ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ አስቀድሞ የጌታችንን ትምህርቶች በአረማይክ ቋንቋ ሎጂያ በተባለ መጽሐፍ ሰብስቦት ነበር።በኋላም ወንጌሉን ሲጽፍ የጌታችንን ትምህርቶች የገለበጠው ከዚህ መጽሐፍ ነው

በግሪክ፤- አብዛኞቹ ጥንታውያን ቅጂዎች የሚገኙት በግሪክ ቋንቋ በመሆኑ በግሪክ ቋንቋ ተጻፈ የሚል ሀሳብ አለ።

የማቴዎስ ወንጌል ከማርቆስ ወንጌል ቀጥሎ በሁለተኛነት ተጽፎ እያለ የመጀመሪያውን ተርታ ያገኘበት ዋናው ምክንያት አቀራረቡ ለብሉይና ሐዲስ ኪዳን ድልድይ ስለሆነ ብሉይ ኪዳን ትንቢትና ምሳሌ በሐዲስ ኪዳን መፈጸሙን ስለሚያሳይ ነው። ወንጌሉን የጻፈው በምድረ ይሁዳ ተቀምጦ ሳለ በሶሪያ ውስጥ የሚገኝ በአንጾኪያ ከተማ ነው።

- ❖ የቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል የተጻፈበት ምክንያት

ሀ. አይሁድ ጌታን በድንግልና አልተወለደም ብለው ስለነበር እመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ያለአባት መወለዱን ለመመስከር

ለ. ኦሪትን ሊሽር መጣ ብለውት ስለነበር ኦሪትን ሊፈጽም እንጂ ሊሽር አለመምጣቱ ለማስረዳት

ሐ. ቡበሉይ ኪዳን ስለመሲሕ መምጣት የተነገሩ ትንቢቶች በኢየሱስ ክርስቶስ እንደተፈፀመ ለመግለፅ

1.2 የቅዱስ ማርቆስ ወንጌል

እናቱ ማርያም አባቱ አርስጦቡሎስ ይባላሉ።የማርቆስ እናት ማርያም ባውፍልያ ቤቷን ለክርስቲያኖች መሰብሰቢያነት የሰጠች ደግ ሴት ነበረች።ጌታም የመጀመሪያውን የሐዲስ ኪዳን ቁርባን ለሐዋርያት ያቆረባቸው በእርሷ ቤት ነው።በበዓለ ሃምሳም መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት የወረዳላቸው በእርሷ ቤት ተሰብስበው ሲጸልዩ ነው።ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር ከታናሿ እስያ እስከ ሮም ድረስ ሰብከዋል።በጫማ ሠፊው በአንያኖስ አማካኝነት የመጀመሪያው የግብፅ ቤተክርስቲያን በአናንያኖስ ቤት

ተመሠረተች።በግብፅ ቤተክርስትያን የትንሳኤን በዓል ሲያከብር ጣዖት አምላኪዎች ተነስተውበት በማሰርና በማንገላታት ከተሰቃየ በኋላ ሚያዚያ 30 ቀን ዐረፈ።

የቅዱስ ማርቆስ ወንጌል ከወንጌላት ሁሉ አጭሩ ወንጌል ነው።16 ምዕራፎችም ይዟል።ወንጌሉን የፃፈው ለሮማውያን በመሆኑ ከሌሎች ወንጌላውያን (ቅዱስ ማቴዎስና ዩሐንስ) የተለየ አገላለጥና አፃፃፍ ተጠቅሟል።የተፃፈት ቋንቋ ሮማይስጥ ነው።ቅዱስ ማርቆስ ወንጌሉን የፃፈው ለአረማውያን በመሆኑ የአረማይክን ቃላትና የዕብራውያንን ባህል ሊያውቁት ስለማይችሉ ተርጉሞ አስቀምጦላቸዋል።ለምሳሌ፡-

- ቦአኔርጌስ፡- የነጎድጓድ ልጆች(3፥17)
- ጣቢታ ቁሚ፡- አንቺ ብላቴና ተነሽ(5፥41)
- ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ፡- አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ

❖ የማርቆስ ወንጌል የተጻፈበት ምክንያት

- ከሮማውያን(ከአሕዛብ) ወገን ወደ ክርስትና ሃይማኖት ተመልሰው ላሉ በሃይማኖት በምግባር እንዲጸኑ
- ሮማውያን(አሕዛብ) አማልክቶቻቸውን የሚያውቋቸው በኃይላቸው ስለነበር በወንጌሉ የኢየሱስ ክርስቶስን ኃያልነት፣የአለም ሁሉ ንጉሥና ፈጣሪ መሆኑን እንዲሁም የማዳን ሥራውን በመግለጽ ያላመኑትን ለማሳመን ጽፏል።አንዳንዴ የላቲን፣የአረማይክና ሌሎችንም ቃላት ትርጉማቸውን ለማስረዳት ጽፎላቸዋል።

1.3 የቅዱስ ሉቃስ

ቅዱስ ሉቃስ ወንጌላዊ ሀገሩ አንጾኪያ ሲሆን በአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከተነሱት ቅዱሳን አንዱ ነው።ቅዱስ ሉቃስ የሕክምና ሙያውን (ቆላ 4፥14) ያጠናው ከአቴናና ከእስክንድሪያ ነው።የሥነ ስዕል ችሎታም ነበረው።ቅዱስ ሉቃስ በሰማዕትነት እስካረፈበት ሰዓት ድረስ የቅዱስ ጳውሎስ ደቀመዝሙር በመሆን አገልግሎታል። (2 ኛጢሞ 4፥11)

ቅዱስ ሉቃስ በድልማጥያ ወንጌልን በመስበክ ላይ እያለ አይሁድና ካህናተ ጣዖት ተባብረው ትምህርቱን በመቃወም ተነሱበት። መስከረም 20 ቀን 58 ዓ.ም አይሁዳና አረማውያን ጉባኤ አድርገው ነገር በመሥራት ለንጉስ ከሰሱት።እሱን ለመያዝ 200 ወታደሮች በተላኩበት ወቅት በመንፈስ ቅዱስ በመረዳቱ ያስተማራቸው የነበሩትን ምዕመናን ወደ የቤታቸው ላከና ወደ ባሕር ተጠግቶ አንድ ዓሣ አስጋሪ ጋር ቀርቦ ወንጌልን ካስተማረው በኃላ በመጨረሻ «እንካ እነዚህ የሕያወትን መንገድ ይምሩሃል»በማለት የያዛቸውን መጻሕፍት ሁሉ ሰጠው።ያም ዓሳ አስጋሪ እጅግ ተደስቶ እቃ በማያስቀምጥበት ቦታ በክብር አኑራቸው።

ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ወንጌሉን የጻፈበት ሀገር አካይያ ሲሆን የጻፈው በግሪክ(ፅርዕ) ቋንቋ ነው።ወንጌሉ የተጻፈው ከ58-60 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ቅዱስ ጳውሎስ በእስር ላይ እያለ ባገኘው እረፍት ነው።ሉቃስ ወንጌል 24 ምዕራፎች የያዘ መጽሐፍ ነው።

የሉቃስ ወንጌል «የአሕዛብ ወንጌል»፣ስባኬ መንፈስ ቅዱስ «ስባኬ ጸሎት»፣«ወንጌለ አንስት»እየተባለ ይጠራል።

- ‹‹የአሕዛብ ወንጌል»፡-እየተባለ የሚጠራው ወንጌሉ የተጻፈው ለአሕዛብ በመሆኑ ነው።
- ‹‹ስባኬ መንፈስ ቅዱስ»፡-ምክንያቱም ስለ መንፈስ ቅዱስ ደጋ ደጋግሞ ይናገራልና
- ‹‹ስባኬ ጸሎት»፡-ከሌሎች ወንጌላት በበለጠ ሁኔታ ደጋግሞ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስና የእመቤታችን ድንግል ማርያምን ጸሎትን ጽፏልና።
- ‹‹ወንጌለ አንሰት»፡-ስለ እመቤታችን ድንግል ማርያም ስለ ቅድስት ኤልሳቤጥ፣ስለ ማርያም አንተ እፍረ ወዘተ በስፋት ይናገራልና።

❖ የቅዱስ ሉቃስ ወንጌል የተጻፈበት ምክንያት

- ✓ በሮም ግዛት ውስጥ የሚኖሩትን ወደ ክርስትና የተመለሱትን ለማጽናት ያልተመለሱትን ደግሞ ለመመለስ ጽፎላቸዋል።
- ✓ ለሮም ባለስልጣን (ለቴዋፍሎስ) ለጥያቄው መልስ ለመስጠት ጽፏል።

ከሁሉም መጻሕፍት በበለጠ ሁኔታ የእመቤታችን ድንግል ማርያምን ፍቅርና እናትነት ለመግለጥ ጽፏል።

1.4 የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል

ቅዱስ ዮሐንስ ሀገሩ የገሊላ አውራጃ ሲሆን ከወንድሙ ከያዕቆብና (ከ12 ሐዋርያት አንዱ የሆነ) ከአባቱ ከዘብዴዎስ ጋር ዓሳ እያጠመደ ይኖር ነበር።እናቱም ከ36 ቅዱሳት አንሰት አንዷ እንደሆነችና ማርያም እንደምትባል የቤተክርስትያን ትውፊት ይመሰክራል።ማቴ **27፣46**

- ❖ የዮሐንስ የተለያዩ ስሞችና ምክንያታቸው

ፍቁረ እግዚእ በኑሮው ጌታን በመምሰል ጌታን ይወደው ስለነበር

ነባቤ መለኮት(ታዖሎጎስ) ነገረ መለኮትን ከሌሎች ወንጌላውያን በበለጠ አምልቶና አስፍቶ በጥልቀት በማስተማሩ

ቦአጌርጌስ(ወልደ ነጎድጓድ) የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት በመግለጡና ለጌታችን ባለው ቅንአት ባሳየው የሀይል ስራ

ባለ ራእይ(አቡቀለምሲስ-በግሪክ) ኃላፍያንንና መፃእያንን በራእይ በመግለፁ

ቁጽረ-ገጽ(ፊቱ በሀዘን የጠቆረ) በእለተ አርብ በእግረ መስቀል ተገኝቶ የጌታችንን መከራ መስቀል በማየቱ ከዚያች እለት ጀምሮ ፊቱ በሀዘን ጠቁሯል

የዮሐንስ ወንጌል ከትረካ ይልቅ ነገረ መለኮታዊ ይዘት ስላለው ከሌሎቹ ወንጌላት ይለያል።ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ከጸራቅሊጦስ በኃላ ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር በኢየሩሳሌም በአንጾኪያ በመቅዶንያ በእስያ ከተሞች በተለይም በኤፌሶን አስተምሯል።ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌሉን፣ 3 ቱን መልእክታትና ራእዩን የፃፉ ሐዋርያ ነው።ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈው ከፍጥሞ ደሴት ሲመለስ በኤጅያን ባሕር ወደብ በ96/98 ዓ.ም አካባቢ ነው።

- ❖ የቅዱስ ዩሐንስ ወንጌል የተጻፈበት ምክንያት

1 ከሶስቱ ወንጌላት የጎደለውን ለመሙላት

2 ቅድመ ዓለም የነበረውን ሥጋን የተዋሐደውን ትንቢት የተነገረለት ሱባኤ የተቆጠረለት መሲሕ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ለመግለጥ ጽፏል።

3 የሰው ልጆች ሁሉ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ መሆኑን አምነው የዘለዓለም ሕይወት የሚያገኙ መሆኑን ጽፏል።

4 የሕይወት አወንጀራ የዓለም ብርሃን የበጎች በር መልካም እረኛ ትንሣኤና ሕይወት መንገድ እውነትና ሕይወት «እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ» የሚለው የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና አምላክነት የሚገልጽ መሆኑን ለማስረዳት ጽፏል።

2 የታሪክ ክፍል (የሐዋርያት ሥራ)

ሐዋርያት የሚለው ቃል የሐዋርያ ብዙ ቃል ሲሆን ሐዋርያ ሖረ ከሚለው የግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን ትርጉሙም ተጓዥ ማለት ነው።ሐዋርያት በአይሁዳውያን ዘንድ አላዋቂ ከሚባሉት የተመረጡ ናቸው።በተልኳቸውም ድውይ ሲፈውሱ ሙት ሲያስነሱ ጋኔን ሲያወጡና የወንጌል ብርሃንነትን ሲመሰክሩ በህዝቡ ዘንድ ሞገስ አግኝተው ነበር።የሐዋርያት ሥራ የሚለውን መጽሐፍ የፃፈው ቅዱስ ሉቃስ ነው።በዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ሉቃስ ሐዋርያት ያደረጉትን ሥራ በሰፊው ፅፏል።ሥራውንም የሚሰራው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነም ያስረዳል።

የቅዱስ ሉቃስ ዓይነተኛ ሐሳብ ሐዋርያት የኢየሱስ ክርስቶስን ትእዛዝ እየፈፀሙ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ወንጌል ለአለም እንዳዳረሱ ለማስረዳት ነው።ይህ መጽሐፍ እውነተኛ የክርስትና ጠባይን ስለሚገልፅ የተለየ የክርስትና መጽሐፍ ይባላል።ይኸውም ከመጀመሪያው አንስቶ እስከ ዕርገቱ ከፃፈ በኃላ ከጸራቅሊጦስ ጀምሮ የመጀመሪያውን የቤ/ክ መሰረትና ሁበረት፣የቤ/ክንን ታምራት ፣ የመጀመሪያውን ጥምቀት ፣ የመጀመሪያውን የቤ/ክ ስደት ፣የመጀመሪያዎቹን ሰማዕታት ፣ የመጀመሪያውን ሐዋሪያዊ ጉዞ ከአይሁድ አለም ወጥቶ ወደ አሕዛብ መሄዱን ፣ የመጀመሪያዎቹን የዲያቆናት ምርጫና ሹመት የሚያስረዳ ከመሆኑም በላይ ቤ/ክ ከምን ተነስታ ከምን እንደደረሰች የሚያሳይ ከፍተኛ ጠቃሚነት ያለው መጽሐፍ ነው።

- ❖ የሐዋርያት ሥራ የተጻፈበት ምክንያት
- ➢ የቅድስት ቤ/ክን አመሰራረትና ዕድገት ለመግለፅ
- ➢ የርደተ መንፈስቅዱስን ሁኔታ ለማስረዳት
- ➢ ቅዱሳን ሐዋርያት የኢየሱስ ክርስቶስን ትእዛዝ በመፈፀም ወንጌልን በአራቱም አቅጣጫ እንዳዳረሱ በመግለጥ የቅዱሳን ሐዋርያትን ሃይማኖትና ተግባር(ሥራ) እንድንከተል እውነተኛ የክርስትና ጠባይን ለማሳወቅ ፅፏል።የሐዋርያት ሥራ 28 ምዕራፎች አሉት

3 የሥርዓት ክፍል

ሥርዓት የሚለው ቃል ሠርዓ ከሚለው የግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን ትርጓሜውም አሰራር ደንብ መርሐ ግብር ማለት ነው። ይህም ሥርዓት በክርስቶስ ደም የተመሰረተች ቤ/ክ አምልኮቷን የምትፈፅምበት ሕዝበ እግዚአብሔርን የምትጠበቅበት ጸጋ የሚያሰጥ ቅዱስ ሥርዓት ነው።የቤ/ክ እምነቷ ብቻ ሳይሆን ሥርዓቷም እግዚአብሔር በቅዱሳት መጻሕፍት የገለጠው ቅዱስ ሥርአተ አምልኮ ነው።የ/ኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የእለት ተእለት መንፈሳዊ አገልግሎት የምትፈፅምበት የሥርዓተ ቤ/ክ መጻሕፍት አሏት።እነዚህም መጻሕፍት ሐዋርያትና ሊቃውንት በየጊዜው ለቤ/ክ መተዳደሪያ የወሰኑትና የደነገጉት ነው።

- ❖ የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ምንጮች
- የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት
- የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት
- የሊቃውንት መጻሕፍት
- ቀኖናወ አበው(የአበው ቀኖና)
- የሥርዓት መጻሕፍት ወ.ዘ.ተ. ናቸው።

ሥርዓትን መጠበቅና በሥርዓት መኖር አስፈላጊ እንደሆነና መንፈሳዊ ግዴታም እንዳለብን ዋነኛው የሥርዓት ምንጭ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል።ለምሳሌ «...ምድርም ከሚቀመጡባት በታች ረክሳለች ሕጉን ተላልፈዋልና ሥርዓቱንም ለውጠዋልና» ት.ኢሳ **24÷5**

‹‹...ከሥርዓትህ የሚርቁትን አጎሳቆልካቸው» መዝ **118÷118**

‹‹...ያለሥርዓት የሚሔዱትን ገስጸቸው» **1** ኛተሰ **5÷14**

‹‹...ያለሥርዓት ከሚሔድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርክቶስ እንለምናችኃለን» **2** ኛተሰ **3÷6** በማለት የሥርዓትን አስፈላጊነትና ለሥርዓት ሊሰጥ የሚገባውን ክብር ገልጸውልናል።

የቅድስት ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መጻሕፍትን በሐዋርያት ቅዱስ ሲኖዶስ የተደነገጉ ናቸው።ሲኖዶስ ማለትም ስብሰባ ወይም ጉባኤ ማለት ነው።ይህም ሐዋርያት ከክርስቶስ ዕርገትና ርደተ መንፈስ ቅዱስ በኋላ ተሰብስበው የሰሯቸውንና የደነገጓቸው ቀኖናዎች ናቸው።

❖ መጻሕፍቱ የተጻፉበት ቋንቋ

ስምንቱ የሥርዓት መጻሕፍት በመጀመሪያ የተፃፉበት እናት ቋንቋ ሱርስት (የሶርያ ቋንቋ) ነው።አንዳንድ ሊቃውንት ደግሞ በኋለኛ ዘመን እነዚህ የሕግና የሥርዓት መጻሕፍት በየቋንቋው ለመተርጎም መነሻ ሆነው ያገለገሉት ሰነዶች በሙሉም ሆነ በከፊል ተቀርጸው የተገኙት በግሪኩ ቋንቋ ስለሆነ መጻሕፍቱ በመጀመሪያ የተጻፉት በግሪክ /ልሳነ ጽርዕ/ ነው ይላሉ። ሱርስቱንና ግሪኩን መሠረት በማድረግ ወደ ላቲን(ሮማይስጥ)፣ ቅብጥ(ሳደቅና ማምፊቲቅ)፣ ዐረብኛና ግዕዝ ቋንቋዎች በተለያዩ ተርጓሚያን ተተርጉማል።/ፍትሐ ነገሥት መቅድም/

❖ የሥርዓት ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት አከፋፈል

ሐዋርያት የሠራቸው የሐዲስ ኪዳን የሥርዓት መጻሕፍት ስምንት ሲሆኑ እነርሱም በአጠቃላይ በሦስት ይከፈላሉ። አከፋፈላቸውም እንደሚከተለው ነው።

- ✓ መጽሐፈ ዲዲስቅልያና አራቱ መጽሐፍተ ሲኖዶሳት(ትዕዛዝ፣ግፅው፣አብጥሊስና ሥርዓተ ጽዮን)ሐዋርያት በየጊዜው እየተሰበሰቡ ያዘጋጇቸው መጽሐፍት ናቸው።
- ✓ ሁለቱ ኪዳናት(መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊና ካልእ) ጌታችን ከትንሳኤው በኋላ የተናገራቸው ናቸው።
- ✓ መጽሐፈ ቀለሜጦስ በሮም በኤጲስ ቆጶስነት ተሹሞ የነበረው የቅዱስ ጴጥሮስ ደቀመዝሙር ቀሌሜንጦስ የፃፈው መጽሐፍ ነው። (ፊሊ 4፥3)

በፍትሐ ነገሥት መጽሐፍ እንደተገለጠው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ቁጥር 46 ሲሆኑ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ደግሞ ስምንቱን የትምህርትና የሥርዓት መጻሕፍትን ጨምሮ 35 ናቸው።

3.1 መጽሐፈ ትእዛዝ

ትእዛዝ ማለት በቁሙ ከስራ አስቀድሞ የሚሰጥ የሚጻፍ የሚነገር ሕግ ሥርዓት ወይም አድርግ አታድርግ የሚል ፊቃድና ደንብ ነው።የመጽሐፈ ትእዛዝ ምልክቱ ወይም በአዕዕሮተ ቃል ልዩ መጠሪያው ረስጡብ በመባል ይታወቃል።ትእዛዘ ሲኖዶስ ከ **72** በላይ አንቀጾች ሲኖሩት እነዚህም

- ➢ ሊቃነ ጳጳሳት ሥርዓተ ሲመት አተገባበር
- ➢ ስለ መስዋእት አቀራረብ
- ➢ ስለ ንዋየ ቅድሳት ክብር
- ➢ ሰለ ሥርዓተ ጥምቀት
- ➢ ሰለ ሥጋ ወደሙ ክብር ወ.ዘ.ተ...የሚናገር መጽሐፍ ነው።

3.2 መጽሐፈ ግጽው

ግጽው ማለት በቁሙ የታየ የተለጠ ጉልህ ማለት ነው።ሐዋርያት ለቀሌምንጦስ የሰጡት ሁለተኛ መጽሐፍ ነው።የዚህ መጽሐፍ መሪ ምልክት ረስጠጅ በመባል እንደሚታወቅ ፍትሐ ነገስት ይናገራል።

መጽሐፉ የእግዚአብሔርን ሕልውና በማስረዳት ጀምሮ ሰለምሥጢረ ሥጋዌ ኢየሱስ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም ሰለማስተማሩና ስለሠራቸው ሥራዎች ይናገራል።መጽሐፉ 57 ያህል አንቀጾች ያሉት ነው።

3.3 መጽሐፈ አብጥሊስ

አብጥሊስ የመጽሐፍ ስም ሲሆን ትርጉሙ ቀኖና ማለት ነው።46 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትንና 35 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን በአጠቃላይ 81 መጻሕፍትን ሙሉ ዝርዝር ይዞ ይገኛል።

የአብጥሊስ መለያ መጠሪያው ወይም መሪ ምልክቱ ረስጠአ(ረስጣ) በመባል ይታወቃል።መጽሐፉ የሚናገረው ስለ ኤጲስ ቆጶሳት ሰለካህናት ሰለ ዲያቆናትና ምእመናን አጠቃላይ የስራ ድርሻና መንፈሳዊ ህይወት፣በስፋትም ሰለ ምስጢረ ንስሐ አሰጣጥና አተገባበር የሚያስረዳና የትምህርተ ሃይማኖትን የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊነትና ምንነት የሚያትት ነው። 82 አንቀፆች አሉት

3.4 መጽሐፈ ሥርዓተ ጽዮን

ሥርዓተ ጽዮን ቀኖናተ ሐዋርያት ወይም ትምህርተ ሐዋርያት ከሚባሉት የሐዋርያት ሲኖዶስ መካከል አንዱ ነው። ሐዋርያት ለስብከተ ወንጌል ወደ ዓለም ከመላካቸው በፊት በጽርሐ ጽዮን ተሰብስበው የሠሩትና የደነገጉት የቤተክርስትያን ሥርዓት ሕግና ትምህርት ነው።

የሥርዓተ ጽዮን መጽሐፍ መጀመሪያ የተጻፈበት ቋንቋ ጽርሕ ሲሆን በኋላ ግን ወደ አርበኞችና ወደ ግሪክ ቋንቋዎች ተተርጉሟል።የሥርዓተ ጽዮን መሪ ምልክቱ «ዓይን» ነው።የሥርዓተ ጽዮን ቀኖና መጽሐፍ የሚገልጸው ስለ በዓለ አስተርእዮ(ኤጲፋንያ) ስለ እሁደ ሰንበት በዓል አከባበር ስለ ገሐድ ጾም ወዘተ ያትታል።የቀኖናቱ ብዛትም 30 የሚደርሱ ናቸው።

3.5 መጽሐፈ ኪዳን

ኪዳን ማለት ውል ስምምነት የፍቅርና የአንድነት መሀላ ሰላማዊ ህግ ትምህርት ምስጋና ሁለቱን ወገን (እግዚአብሔርንና ሰውን/ሰውንና ሰውን) አንድ የሚያደርግ ነው።ለሰው ረብና ጥቅም የሚሆን በተስፋ የቆሙ ቢጠብቁት በረከት የሚያሰጥ ቢያፈርሱት ደግሞ ጉዳትና ጠብ የሚያመጣ ብዙ በረከትም የሚያሳጣ ነው። (ገላ 3÷15)

መጽሐፈ ኪዳን የኢየሱስ ክርስቶስና የሐዋርያት ቃል ከትንሳኤ - እርገት ያስተማራቸውና እየጠየቁት የመለሰላቸው ነው።ይህም ከእርገት በኋላ በጥንተ ስብከት ሐዋርያት ጽፈውታል።

ጌታ በመዋዕለ ሥጋዌ ሳለ ያስተማረው ወንጌል ሲባል ከትንሳኤው እስከ እርገቱ ያስተማረው ደግሞ ኪዳን ይባላል። ከሞተ በኋላ ተነስቶ ሰለምን ኪዳንን አስተማረ ቢሉ በመዋዕለ ሥጋዌው በፈቃዱ ለሰው ልጅ ድህነት ወንጌልን እንዳስተማረ ከሞተም በኋላ ተነስቶ ለሰው ልጅ ድህነት በፈቃዱ ኪዳንን አስተምሯል።መጽሐፈ ኪዳን የተባሉትም ሁለት መጽሐፍት ናቸው።

ሀ.መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ

‹‹ይህን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የኪዳን መጽሐፍ የሐንስ፣ጴጥሮስና ማቴዎስ እያጻፋቸው ጻፉት በዚህም ዓይነት መግለጫም ወደ ኢየሩሳሌም ላከው።»

መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ 59 አንቀጾች ያሉት መጽሐፍ ነው።ይህም ሰለ ስርዓተ ቤተ ክርስቲያን የዘወትር ኪዳናት ትምህርተ ኅቡአት እግዚአብሔር ዘብርሃናት ቅዳሴ እግዚእ በእንተ ቅድሳት ወ.ዘ.ተ...የሚናገር መጽሐፍ ነው።

የመጽሐፉ ኪዳን ቀዳማዊ ይዘት ሥርዓተ ጸሎትና ሥርዓተ ቅዳሴ ነው። ይህም ጸሎተ ኪዳን ዘእግኢ፣እንዲጸልዩ በተመደቡ ሶስት የኪዳን ጊዜያት(ጸሎተ ኪዳን ዘሰልስቱ ጊዜያት) ተከፍለው የሚገኙ ዘጠኝ ሥርዓተ ጸሎታትን (ዘጠኙ ኪዳናት የሚባሉትን) ይዟል።እነርሱም፡-

1.ኪዳን ዘመንፈቀ ሌሊት

ሀ.ለከ እግዚኦ ለገባሬ ኩሉ

ለ.አምላከ ብርሃን ለገባሬ ሕይወት

ሐ.ንሴልስ ለከ ዘንተ ስብሐት

2.ኪዳን ዘነግህ

ሀ.እግዚአብሔር አብ ወሃቤ ብርሃን

ለ.እግዚኦ ኢየሱስ ክርስቶስ ስምዓነ ቅዱስ

ሐ.ንሴልስ ለከ ቅዱስ ስብሐት

3.ኪዳን ዘሠርክ

ሀ.ለከ ለአብ ዘኢይማሰነ መድኃኔ ነፍስነ

ለ.ንቄድሰከ እግዚኦ

ሐ.ለከ ዘእምልብነ ናቸው

ለ መጽሐፈ ኪዳን ካልዕ

እንደ መጀመሪያው የኪዳን መጽሐፍ በአንቀጽ የተከፋፈለ አይደለም።በሥርዓት ቅዳሴው መጽሐፍ የቅዳሴ እግዚእ መግቢያ ላይ እንደተገለጸው መጽሐፈ ኪዳን ካልዕ ደግሞ ወጥ ሆኖ ስለ ካህናት ሹመትና አገልግሎት ስለ ንዑስ ክርስቲያን ጥምቀትና ምሥጥረ ቁርባን እንዲሁም የሐሳዊ መሲሕን የጥፋትን ነገር በመግለጽ ስለ ክርስቶስና ስለ ዳግም ምጽአት የሚናገረ መጽሐፍ ነው።በአጠቃላይ የመጽሐፈ ኪዳን ካልዕ መጽሐፈ ስለሐሳዊ መሲሕና ተከታዮች በይበልጥ በስፋት ይናግራል።

3.6 መጽሐፈ ዲድስቅልያ

ዲድስቅልያ የመጽሐፉ ስም ሲሆን ትርጉሙም ትምህርት ማለት ነው።ይህም የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ 35 የሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ አንዱና ጥንታዊው ነው። «ዲድስቅልያ ዘቅዱሳን ሐዋርያት» ይባላል። መጽሐፉ ቀድሞ ሲል ወደ ግዕዝ ቋንቋ ተተርጉሞና ተጠብቆ ኖሯል።እንዲያውም ከፍተኛ ዋጋው ቀደም ብሎ ስለታወቀ ከእንግሊዘኛ ትርጓሜው ጋር በአውሮፓ ታትሞል።ይህ መጽሐፍ የቅዱሳን ሐዋርያት አስተምህሮ የሥርዓት ክፍል ሲሆን 43 አንቀጾችን የያዘ መጽበለ ትምህርት ወተግሣጽ ነው።እነዚህም ስለሰው ልጅ ሕይወትና ሞት ስለ ፍቅረስብ እና ፍቅረእግዚአብሔር ስለ ምሥጢረ ጥምቀት ስለጸምና ጸሎት ሰለ ምሥጢረ ቁርባን ሰለ ካህናት ክብርና አገልግሎት ሰለ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንና እንዲሁም በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ላይ ሰለሚፈፀሙ የተለያየ ምስጢራት ይናገራል። መጽሐፈ ዲድስቁልያ አበይትና ንዑሳን አንቀጾች አሉት።በእያንዳንዱ አብይ አንቀጽ ውስጥ ብዙ የተለያዩ ንዑሳን ክፍሎች ይገኛሉ።

3.7 መጽሐፈ ቀሌሞንጦስ

መጽሐፉ ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ ስለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውና ቅዱስ ቀሌሞንጦስ ከእርሱ አግኝቶ የጻፈው ነው።የቀሌሞንጦስ መጽሐፍ በአዕጽሮተ ቃል ልዩ መጠሪያው ”ጴጥ” ሲሆን ትርጉሙም ጴጥሮስ ማለት ነው ይዘቱም ሥርዓተ ቅዳሴያዊ ቅርጹን አስመልክቶ ስለጽላት ኪዳን ቡራኬ ማለትም በኤጲስ ቆጶስ አዲስ

ቤተመቅደስ የሚባረክበትን ሥርዓት ሥርዓተ ጥምቀትና በእጅ መንሻና መተያያ ጥምቀት እንደማይፈቅድ ስለሥርዓተ ቁርባን ወዘተ ይናገራል። በቀኖናዊ ክፍሉም ስለ ሰማዕታትና ስለ ክ በዓላት ስለ ሰንበተ ክርስቲያን የእረፍተ ቀን መሆን በሰሙነ ሕማማት ምዕመናን ከተግባረ ሥጋ ማረፍ ግዴታ ስለመሆኑ ያትታል።/ቀኖና ፭-፲፭/ በትውፊትም ቅዱስ ቀሌምንጦስ የሮማ ጳጳስ መሆኑ ይነገራል። ድህረ ልደተ ክርስቶስ የፃው ቀዳማዊ ቀሌምንጦስ የቤተ ክርስቲያን አበው መምህራን በመገደላቸው ምክንያት አለመግባባት ወደተፈጠረበት የቆሮንጦስ ቤተ ክርስቲያን በሮማው ጳጳስ መልእክት ነው።መልእክቱ የ 70 ው ሊቃናት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተናገራቸውና እንዲሁም ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት በተለይ ከዕብራውያን መልእክት የተወሰደ መሆኑ ተገልጿል።

- ❖ የመጽሐፉ ቀሌምንጦስ ክፍሎች

መጽሐፉ በስምንት ዐበይት ክፍሎች የሚከፈል ሲሆን የእያንዳንዱ ክፍል ሐሳብ በከፊል እንደሚከተለው ቀርቧል።

ክፍል 1

- ➢ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካረገ በኃላ ሐዋርያትን በሁሉም አቅጣጫ እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ እንደያስተምሩ እንደላካቸው
- ➢ ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት ትምህርት ላይ እንደተመሰረተች
- ➢ ከአዳም ጀምሮ ስላለው አጠቃላይ የዘር ሐረግ
- ➢ ሰለ ገነትና ሰለታላላቅ አባቶች የቀረበ ሰላምታ(ምስጋና)
- ➢ ከገነት ወጥተው ወደ ደብረ ቅዱስ ሰለ ገቡ ሰዎች

ክፍል 2

- ➢ ቀሌምንጦስ የቅዱስ ጴጥሮስ ደቀመዝሙር ሆኖ ሰለመመረጡ
- ➢ ሰለቀሌምንጦስ ሕይወትና አጠቃላይ ኑሮው
- ➢ የቀሌምንጦስ መንፈሳዊ አገልግሎት

ክፍል 3

- ➢ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና ለሐዋርያት ያደረገውንና ያስተማረውን ሁሉ ለቀሌምንጦስ እንደነገረው
- ➢ በአገልግሎቱ እንዲጸና እንደመከረው

ክፍል 4

- ➢ እግዚአብሔር ለቅዱስ ጴጥሮስ ስላሳየው ራእይና ተአምራት
- ➢ ሰለሥልጣነ ክህነት ከጳጳሳት እስከ ዲያቆናት አጀማመርና አሰጣጥ
- ➢ ሰለዓለም አፈጣጠርና ሁኔታ
- ➢ ሰለዳግም ምጽአት እንዲሁም ሰለጻድቃንና ኃጥአን ሁኔታ
- ➢ ሰለመንፈስ ቅዱስ መውረድና ሁሉን እንደሚገልጥላቸው ይናገራል

ክፍል 5

- ➢ በሰው ልጆች በሰማይና በምድር ላይ ሰለሚሆነው ነገር ሁሉ ቅዱስ ጴጥሮስ ለቀሌምንጦስ እንደነገረው
- ➢ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤቴልሔም ሰለመወለዱ

- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ግብፅ ሰለመሰደዱ
- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግብፅንና በዙሪያዋ ያሉ አውራጃዎች ከአምልኮተ ጣዖት ነጻ ሰለማድረጉ
- ወደ ገሊላ ሰለመግባቱ ይናገራል

ክፍል 6

- እግዚአብሔር ለሙሴ የነገረው ሥርዓተ ደብተራ ለቅዱስ ጴጥሮስ እንደተነገረው ቅዱስ ጴጥሮስ ደግሞ ለቀሌመንጦስ ይህን ሥርዓት እንዳስተማረው
- ሙሴ እንደ ሊቀጳጳስ ሆኖ አሮንና ልጆቹን ሰለመሾሙ
- ቅዱስ ጴጥሮስ ለቀሌመንጦስ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን እንዳስተማረው
- ሰለ ሙሴና ሰለጴጥሮስ ንጽጽራዊ ትምህርት
- በክርስቶስ የሚያምን የክርስቶስን ሥራ እንደሚሰራ
- ቅዱሳን ሐዋርያት ድውያንን ሰለመፈወሳቸው
- ንጽሐና በረከት ለመቀበልም ለመስጠትም አስፈላጊ እንደሆነ
- ክርስቶስ ራሱን ለቤተ ክርስቲያን መስዋእት አድርጎ እንዳቀረበ ይናገራል

ክፍል 7

- ሰለ ክርስቶስ አምላክነትና አዳኝነት
- ሰለዲያብሎስ ክፋትና ሽንፈት
- ሰለ ሙሴ በትርና ሰለ ክርስቶስ መስቀል ምሳሌነት
- ሰለ ቅዱሳን ሐዋርያት አስተምህሮ
- ኖህ መርከቡን እንዲሰራ ሰለመታዘዙ ይናገራል።

ክፍል 8

- ቅዱስ ጴጥሮስ ሰለ ንሰሐ አስፈላጊነት ያለውና ያስተማረው
- ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ብጹእ ሰለመባሉ
- ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ ጴጥሮስ የቃል መሰረትነት እንደምትሰራ
- ቅዱስ ጴጥሮስ የመንግስተ ሰማያትን ቁልፍ ሰለመቀበሉ ወ.ዘ.ተ...ይናገራል
- ማጠቃለያ

በአጠቃላይ ስምንቱ የሐዲስ ኪዳን የስርዓት መጽሐፍት ይዘታቸው በትምህርት፣በትንቢት በይበልጥም በስርዓተ ቤ/ክ ላይ ያተኩራል።

4 የመልእክታት ክፍል

እነዚህ መልእክታት ተብለው የሚጠሩት የሐዲስ ኪዳን ክፍሎች አጠቃላይ የትምህርት መጻሕፍት ይባላሉ።የተጻፉትም ለግል ሰዎች ለቤተሰብ ለቤተ ክርስቲያን ወይም ለማኅበር በቀጥታ ትምህርት ተግሳጽ ምክር መሠረተ ሃይማኖት ሥነ ምግባራዊ ሕይወትን በአጽንኦት የሚገልጹና የሚያስተምሩ ናቸው።

አጠቃላይ መልእክታቱ በሶስት ይከፈላሉ።

- ለማኅበር የተላኩ መልእክታት ሮሜ፣ፊልጵስዩስ ወ.ዘ.ተ...
- ለግል የተላኩ መልእክታት ፊልሞና፣ጢሞቴዎስ፣ቲቶ፣ሁለተኛ የዮሐንስ መልእክት ወ.ዘ.ተ...ናቸው
- ለዓለም አቀፍ መልእክት የዕብራውያን መልእክት (ለእስራኤል ዘሥጋ እስራኤል ዘነፍስ)፣1 ኛ ዮሐንስ መልእክት ወ.ዘ.ተ... ናቸው።

ተ.ቁ	መልእክቱን የፃፉት	ብዛት
1	ቅዱስ ጳውሎስ	14
2	ቅዱስ ዮሐንስ	3
3	ቅዱስ ጴጥሮስ	2
4	ቅዱስ ያዕቆብ	1
5	ቅዱስ ይሁዳ	1
	ጠቅላላ ድምር	21

4.1 የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት

የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ዘመናቸውንና ቅደም ተከተላቸውን ተከትለው ባይጠረዙም የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት 14 ናቸው።የጥራቱም ሁኔታም የሚለያየው እንደመልእክቱ ከባድነትና እንደ የሀገሩ የቤተክርስትያን ታላቅነት ነው። መልክታቱንም በክፍል እንደሚከተለው እንመለከታቸዋለን።

- የመጀመሪያው ክፍል ሁለቱ ወደ ተስሎንቄ የተጻፉትን ይይዛል።እነዚህም በሁለተኛው ሐዋርያዊ ጉዞው በ 52 እና 53 ዓ.ም እንደተጻፉ ይነገራል።እነዚህ መልእክታት ምሥጢረ ምጽአትን በሚመለከት የሚናገሩ ናቸው።
- ሁለተኛው ክፍል ሁለቱን የቆሮንጦስ መልእክታትንና የገላትያን የሮሜን መልክታት ይይዛል።እነዚህ በ 3 ኛው የሐዋርያው ጉዞው በ 56 እና በ 58 ዓ.ም መካከል የተጻፉ ናቸው።በነዚህም ጊዜ አይሁድ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ቤተ ክርስቲያንን የተቃወሙበትን የጳውሎስንም ዛፍ ሆነ ብለው ያበላሹበት ጊዜ ነበር።
- ሶስተኛው ክፍል ቅዱስ ጳውሎስ የመጀመሪያው የሮም እስራቱ ጊዜ በ 62 እና በ 63 ዓ.ም የተጻፉ ናቸው።እነዚህም ወደ ፊሊጵስዩስ ወደ ኤፌሶን፣ወደ ቆላስይስና ወደ ፊልሞና የተጻፉ መልክታት ናቸው።እነዚህ ስለክርስቶስ ማንነት አስፋፍተው የሚናገሩ ናቸው።
- አራተኛው ክፍል በመጀመሪያ ከእስራት የተፈታበት ከ 63-68 ዓ.ም የተጻፉት 1 ኛና 2 ኛ ጢሞቴዎስና ቲቶን ይይዛል። እነዚህ መልእክታት የካህናትን ተግባርና የጠባቂዎችንም ኃላፊነት ስለሚገልጡ የጠባቂነት መልክታት ይባላሉ።የቅዱስ ጳውሎስ መልክታት የይዘት ተመሳሳይነት አላቸው።ይኸውም የሚያመለክተው በአንድ መንፈስ ገላጭነት መጻፋቸው ነው።የመልክታቱም ጠባይ አጠቃላይ 6 ክፍል አለው።

ሰላምታ፡-በሰላምታ አገላለጡ ሰፊ ትምህርት ስለሚገኝበት የመሳብ የማቅረብ ወገንም የማድረግ ኃይል አለውና በሰላምታ መጀመርን ተግባር አደረገው።የሰላምታ አሰጣጡ «ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን» የሚል ነው።ይኸውም የዕብራውያን ሰላምታ በክርስቶስ የሚሰጠውን ጸጋ እንደሚያገኙ የሚያነቃቃ ነው።

ምስጋና፡-ወደ ዋናው ርእሱ ከመግባቱ በፊት ስለ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ስጦታው እግዚአብሔርን አመስግኖ ጽሑፉን ይቀጥላል።

መሠረት ሃይማኖትን ማሳወቅ፡-እንደሚጽፍበት ምክንያት ይለያል እንጂ የያዘውን ርእስ አተኩሮ የርእሱን ዓላማ አስፋፍቶ ይገልጣል።እንዲሁም መልክቱን ለመጻፍ የተነሳሳበትን ምክንያት በመከተል ሰፊ ትምህርት ሃይማኖት ይሰጣል።

ተግባራዊ ትምህርት፡-የክርስትና ምግባር እንዴት መሆን እንደሚገባው አስረድቶ በግልጥ ይፅፋል።ሃይማኖትንና ምግባርን በማዋሐድ ያስተምራል።

ለግል ሰዎች፡-ለጳውሎስ የፍቅሩ መግለጫ ለእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን አባል የሚሰጠው አክብሮትና አገላለጥ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን እንዴት የሁሉ እናት እንደሆነች የሚያስረዱ ምልክቶች ናቸው።

የራሱ መሆኑን ማረጋገጥ፡-በዚህ ዘመን ይተላለፍ ከነበሩት የሐሰት መልእክታት ለመለየት የሚገለጥበት መንገዱ ነው። ይኸውም «ይህን ሰላምታ በገዛ እጄ የጻፍሁት እኔ ነኝከእኔ መልእክት ሁሉ የሚገኘው ምልክት ይህ ነው።የምጽፈውም እንዲህ ነው፣የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን» በማለት መልእክቱ የራሱ መሆኑን በግልጥ ያስረዳ ነበር።

1 ወደ ሮሜ ሰዎች

ሮም ጥንት ሮምየ ትባል ነበር።አሁን የኢጣልያ ዋና ከተማ ስትሆን በቀድሞ ዘመን ግን ለሚታወቁት አገሮች ሁሉ ርዕሰ ከተማ ነበረች።መደበኛ ቋንቋቸው ግሪክ በመሆኑ ኢሊኖርሚስ ወይም የግሪክና የሮም አገዛዝ እየተባለ ይነገር ነበር።

የንጉሰ ነገሥት ከተማ ስለሆነች የልዩ ልዩ ሰዎች መናገሻ አድርገው በተለይም አይሁዶች ምኩራብ ሰርተው ሃይማኖታቸውን አጽንተው ብዙ አሕዛብ እየመለሱ ይኖሩ ነበር።

- ❖ የክርስትና ሃይማኖትም ፈጥኖ ወደ ሮም የገባው
- ➢ ቅዱስ ጳውሎስ ከሮም ጋር ከፍተኛ ግንኙነት ካላቸው ሀገሮች እንደ ኤፌሶን ቆሮንቶስ ተስሎንቄ አቴና ባሉት ከተማዎች ትምህርቱና ተአምራቱ ተረድቶ ነበር።ከእነዚህም ሀገሮችም ሰዎች ሮም ሲሄዱ ትምህርቱንና ክርስትናውን ለሌላው ያስረዱ ስለነበር ነው።
- ➢ በጰንጠቆስጤ(መንፈስ ቅዱስ በወረደበት) ዕለት በግል ፍላጎታቸው በኢየሩሳሌም ተሰብስበው ከነበሩት ሮማውያን አይሁድ ውስጥ የቅዱስ ጴጥሮስን ስብከት ሰምተው አምነው ተጠምቀው ሄደው ቤተክርስቲያን ሮም ውስጥ ያቋቋሙ ሰዎች ስለነበሩ
- ➢ ቅዱስ ጴጥሮስ ሮም ገብቶ ሲሰብክ ስለነበር

ቅዱስ ጳውሎስ በ52 ዓ.ም ከአቴና ወጥቶ ወደ ቆሮንቶስ በሄደ ጊዜ በቀላውዲዮስ ቄሳር አዋጅ ከሮሜ ተሰደው የመጡ አቂለንና ሚስቱን ጵርስቅላን አገኘ።ከእነርሱም ጋር አንድ ዓመት ከሰድስት ወር በዚሁ በቆሮንቶስ ቆየ። አቂላና ጵርስቅላ በሮሜ ስለሚገኙ ክርስቲያኖች ለቅዱስ ጳውሎስ ነገሩት። ቅዱስ ጳውሎስ መልእክቷን ሲጽፍ ከሮሜ ክርስቲያኖች መካከል የሚያውቋቸው ስላልነበሩ አቂላንና ጵርስቅላ ከከተማዋ ክርስቲያኖች ታዋቂ የሆኑትን የአንዳንዶቹን ስም ሰጥተውት መልእክቲቱን አዘጋጅቶ የክንክራኦስ ቤተ ክርስቲያን ዕቃቢት በነበረችው በፊበን እጅ በ54 ዓ.ም አካባቢ ላካቸው። ሮሜ **16÷1**

- ❖ የሮሜን መልእክት የጻፈበት ምክንያት
- ✓ ሮም ውስጥ የሚኖሩት ክርስትናን የተቀበሉት ወንጌል የሞታስተምረውን ፍቅርና ስላሞ ትተው በሥርዓት በባሕል አይሁድና አሕዛብ ባለመስማማት በጭቅጭቅ ይኖሩ ነበር።ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሲሰማ ሁለቱን ወገኖች ለማስታረቅና በክርስትና እምነት ትምህርት እንዲኖሩ ለማድረግ መከፋፈል እንዳይኖር ይህችን መልእክት ጽፎላቸዋል።ሮሜ **1÷5-7**

- ✓ አንዳንድ የክርስትና እምነት ጠላቶች የሆኑ ክርስትያኖች በመንግስት ላይ ያምጻሉ ግብርም አይከፍሉም እያሉ የሀሰት ወሬ እያወሩ ክርስትያኖችን በስጋ ለተሾሙ ሁሉ እንዲገዙ (እምነታቸውን እስካልነኩባቸው ድረስ) በነፍስ ግን ለክርስቶስ መገዛት እንደሚገባ ለማስረዳት ጽፎላቸዋል።ሮሜ **13÷5-7**
- ✓ ወደ ሮም እነርሱን ለመጎብኘት ከመሄዱ በፊት እየተማሩ እንዲቆዩና የጉዞውን ሁኔታም ለማመቻቸት ጽፎላቸዋል።

2.*የመጀመሪያይቱ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች*

ቆሮንጦስ የአካያ ሁለተኛ ከተማ ስትሆን የምትገኘውም በግሪክ ውስጥ ነው።ይህች ከተማ ስመ ጥርና ታላቅ በንግድም የታወቀች የሀብታሞች መናኸሪያ ነበረች።ለምስራቁና ለምዕራቡ አለም ለንግድ አመቺ ስለሆነች የበለጸገች አገር ነበረች። በልዩ ልዩ አገሮች ከመጡ ህዝቦች ጋር ኗሪው በጣም ይበዛ ነበር።

- ❖ *መልእክቱን የጻፈበት ምክንያት*
- ✓ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አስተምሮ ከሄደ በኋላ ከእስክንድርያ የመጣው አይሁዳዊ አጵሎስ ተጠምቆ ለአይሁድ ብሉይን ከሐዲስ እያስማማ ጥልቅ ጠንካራና ምስጢራዊ ትምህርቱን ሲያስተምር ብዙዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣት ጀምረው ነበር። በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘመንም ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው የጌታችንን ትምህርቱን የሰሙት ተአምራቱን ያዩት እንዲሁም በኢየሩሳሌም እያሉ በቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት አምነው የተጠመቁ ብዙዎች ነበሩ።እነዚህ በልዩ ልዩ ምክንያት ያመኑ ክርስትያኖች የሐሳብ መለያየትና የወገንተኝነት ስሜት ሰለጠናባቸው ከዚያም «እኔ የጳውሎስ ነኝ እኔ የጴጥሮስ ነኝ እኔ የአጵሎስ ነኝ»እያሉ ሲከፋፈሉና ሲለያዩ ክርስቶስ ተከፍሏልን? ጳውሎስስ ስለናንተ ተሰቅሏልን?ወይስ በጳውሎስ ስም ተጠመቃችሁን?በመካከላችሁ መለያየት እንዳለ እሰማለሁ **(1** ኛቆሮ **1÷12፣11÷17)** መለያየት ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን የማይበጅ ነው።በማለት ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ችግር ከቀለዮጳ ቤተ ሰዎች ሲሰማ ይህችን *የመጀመሪያ* መልእክቱን ጻፈላቸው።
- ✓ ከአምልኮ ጣዖት ከተመለሱ በኋላ የቆሮንቶስ ሰዎች የቀድሞ የአምሎኮ ጣዖት ባህላቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዓትና ትውፊት በመቀላቀል ይኖሩ ነበር።ለምሳሌ ወደ ቅዳሴ ሲመጡ ሁሉም ለየግሉ ወይንና ጎብስት ይዘው ይመጡና እስኪጠግቡ በልተው እስኪሰክሩ ጠጥተው እየተጨቃጨቁና እየተደባደቡ ቁርባን እንደፈጸሙ ይመስላቸው ነበር።ይባስሞ ብለው ወይንና ጎብስት ማምጣት ያልቻሉ ድሆችን እንደ እነርሱ አሳብ እንዳይቆርቡ ይከለክሏቸው ነበር።ቅዱስ ጳውሎስ ከጌታና ከቅዱሳን ሐዋርያት ያገኘነውን ሃይማኖት ሥርዓትና ትውፊት አብራርቶ ይመክራቸው ዘንድ ይህችን መልእክት ጻፈላቸው።
- ✓ የቆሮንቶስ ሴቶች ወደ ፍርድ ሸንጎ ገብተው ሳይከናነቡ ያለሥርዓታቸውና ያለባህላቸው ለባሎቻቸው እያገዙ መሚገትን አዲስ ወግና ሥርዓት አድርገው ከክህናቱ ፈቃድ እየወጡ ቤተ ክርስቲያን ካልሰበክን ካልቀደሰን እያሉ ሲያስቸግሩ በዚህም የተነሳ «ቤተክርስቲያኒቱ ነውረኛ ሴቶች የተሰበሰቡባትና ሥርዓት የሌላት ናት» እየተባለች በዓለማዊያን ዘንድ እንዳትነቀፍ ቅዱስ ጳውሎስ ፀጉራቸውን እንዲከናነቡ ሥርዓቱን ትውፊቱን ጠብቀው እንዲኖሩ ሲል ይህን መልእክት ፃፈላቸው።
- ✓ የቆሮንቶስ ሰዎች በዝሙት ኃጥያት ይታወቁ ነበር።በዚያን ዘመን «ቆሮንቶሳዊ»ማለት ዘማዊ የሚለውን ትርጉም ይዞ ነበር። ቅዱስ ጳውሎስም በእናንተ መካከል ዝሙት እንዳለ ይወራል።የዚያን ዓይነት ዝሙት በአህዛብ እንኳ የማይገኝ።ቆሮ 5÷1 በዚህም ዘማዊና በኃጥያተኛ ትውልድ መካከል በእኔ በቃሌ የሚያፍር ሁሉ የሰው ልጅ ደግሞ በአባቱ ክብር ከቅዱሳን መላእክት ጋር በመጣ ጊዜ ያፍርበታል።ማር 4÷38 እያለ የተማረውን የወንጌሉን ቃል መሰረት በማድረግ ይህን መልእክት ከዝሙት ጠንቅ እንዲጠበቁ ጻፈላቸው።
- ✓ የቆሮንቶስ ሰዎች ችግር በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች እርስ በርስ መቀናናታቸው ነበር። «እኔስ ከማን አንሳለሁ» እያሉ ሁሉም ትንቢት ተናጋሪ ሁሉም ተርጓሚዎች ሁሉም ሰባክያን ሁሉም በልሳን ተናጋሪዎች ስለሆኑ ሁሉም ራሳቸውን ከፍ በማድረጋቸው ጭቅጭቅ ነበር።ለዚህም ሁሉ ችግሮች ክርስቲያናዊ መልሶችን ጽፎ አዘጋጅቶ በጢሞቲዎስ ፣በእስጢፋኖስ በፈርዶናጥስና በአካያቆስ እጅ ይህችን መልእክት በ 54 ዓ.ም ገደማ ላከላቸው። **1** ኛቆሮ **15÷2-58፣1** ኛቆሮ **16÷1-24**

- ✓ በመጨረሻም ቅዱስ ጳውሎስ ጥያቄ አዘል ደብዳቤዎችን ጽፈውለት ነበርና የተለያዩ ችግሮቻቸውን በመጠየቅና መልስ በማዘጋጀት በሃይማኖት ይጸኑ በምግባርም ያድጉ ዘንድ ይህን መልእክት ጻፈላቸው።

3.ሁለተኛይቱ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምእመናን በሃይማኖት ልጁ በጢሞቴዎስ እጅ የመጀመሪያይቱን መልእክት ጽፎ ቢልክላቸውም ከኃጥያት ርቀው ንጽህና ጠብቀው መኖር አልተቻላቸውም።ክፉ ምግባራቸውንም ቀጠሉ ይህን በልጁ የላከውን መልእክት እንዳልተቀበሉትና ተግባራዊ እንደማያደርጉትም በሰማ ጊዜ ከእንግዲህስ እኔ ብሄድ ይሻላል በማለት ወደ ቆሮንቶስ በሄደ ጊዜ እንዳልተቀበሉትና እንዳሳዘኑት በዚህ መልእክት ገልጿል።**2** ኛ ቆሮ **2÷5-11,12÷2** የመጀመሪያ መልእክት ምን ያህል ተግባራዊ እንዳደረጉት ለመርዳት ቲቶን ላከ።**2** ኛ ቆሮ **2÷1-6** ከቅዱስ ጳውሎስ ጋርም በመቄዶንያ ተገኝተው ሲጠይቀው የላካቸው መልእክት ብዙዎችን በክፉ ሥራቸው እንዲጸጸቱ ንስሐም እንዲገቡ እንዲያውም የአባቱን ሚስት ያገባ እንዲለይ አድርገዋል በማለት ደስ የሚያሰኝ ወሬ ነገረው **1** ኛ ቆሮ **7÷5-16** የቲቶን መልእክት ሲሰማ ቅዱስ ጳውሎስ እዚያው በመቄዶንያ እያለ ይህችን ‹‹ሁለተይቱ››የተባለችውን መልእክት ፃፈላቸው።

- ❖ ቅዱስ ጳውሎስ ሁለተኛይቱን መልእክት የጻፈበት ምክንያት
- ✓ ንስሐ ገብተው በመመለሳቸው ለማመስገንና ለማጽናት
- ✓ ከአይሁድ ወገን የሆኑ ሐሳውያን መምህራን ወደ ወጋቸውና ልምዳቸው ለመለወጥ በመሞከራቸው ብዙዎች ተታለው በትምህርታቸውም ተስበው ስለነበር የሐሰተኞች መምህራን ትምህርት ወግና ስርዓት እንዳይከተሉ ለመምከር ፃፈላቸው።
- ✓ ቀድሞ በፃፋቸው መልእክት ተደናግጠው(በተግሣጻጽና፣በምክሩ) ሐዘናቸውም ከልክ ያለፈ ነበር።ከልክ ያለፈ ሐዘናቸውንም ለማስታገስ የመልእክቱን የተገሳጹንና የምክሩን ጠቃሚነት አብራርቶ ጻፈላቸው።
- ✓ ይህች በ55 ዓ.ም አካባቢ በቲቶና ሉቃስ እጅ የተላከችበት ምክንያትም ስለ መልእክቷ እውነተኛነትና ስለቅዱስ ጳውሎስ ህይወት መመስከር የሚችሉ በመሆኑ ሲሆን በመጀመሪያዋ መልእክቱ ተግሳፅ ጠልተውት እንዳይቀሩ የመጀመሪያዋን መልእክትም እንዳያቃልሉ ሁለተኛይቱን የምስጋና ምክር አዘል አድርጎ ፅፎላቸዋል።
- ✓ የእርሱም ሥልጣን ከእግዚአብሔር እንደሆነ ለማስረዳት አብራርቶ ጽፏል።

4.ወደ ገላትያ ሰዎች

ይህች ገላትያ የተባለች ሀገር በታናሿ እስያ አጋርዮስና አሊያስ በተባሉ ሁለት ወንዞች መካከል የምትገኝ አውራጃ ስትሆን ዛሬ የቱርክ መናገሻ ከተማ ናት።ይህች የገላትያ ሰዎች መልእክት የተጻፈላቸው በ 48 ዓ.ም ሲሆን የተላከላቸውም በቲቶ እጅ ነው።መልክቲቱም ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ የመጀመሪያዋ እንደሆነች ይነገራል።ክርስትያኖች በእግዚአብሔር የባህርይ ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ያገኘነውን ጸጋና ክብር ከኃጢያት ባርነት ነጻ እንዴት እንደወጣን የምትናገር የምታስረዳ በመሆኗ ‹‹የነጻነት መልእክት›› በመባል ትጠራለች።

- ❖ ይህን መልእክት የጻፈበት ምክንያት
- ✓ የአይሁድ መምህራን የሐሰት ትምህርት ወጋቸውን ሥርዓታቸውን የገላትያ ሰዎች እንዳይቀበሉ የተማሩትን የሐዋርያት ትምህርት እንዲጠብቁ እንዲጸኑ
- ✓ የአይሁድ መምህራን እንደ ሌሎች ሐዋርያት ጌታን አላየም ከቅዱሳን ሐዋርያትም እኩል አይቆጠርም ይሉት ስለነበር ይህንን የእርሱን ሐዋርያነትና ሥልጣኑን ያውቁ ዘንድ
- ✓ ከሐዋርያት እንጂ ከጌታ ስላልተማረ ክብሩ ያነሰ ሰው እያሉ አይሁድ ካህናት የገላትያን ሰዎች ያወናብዱ ያስጨንቁ ስለነበር ይህን ለማስረዳት

- ✓ መገረዝ ጽድቅን ያስገኛል ጳውሎስ ራሱ ተገርዟል እናንተን ግን ጽድቅ እንዳታገኙ «መገረዝ አይጠቅምም»ይለችኋል እያሉ በዚህ ምክንያት ከእውነተኛዋ ሃይማኖት ሕግና ሥርዓት ያስወጧቸው ስለነበር ይህን ለማስረዳት
- ✓ ሐዋርያት ከአይሁድ ተፋቅረው ሕገ ኦሪትን ጠብቀው ሥርዓተ አይሁድን አክብረው በኢየሩሳሌም እየኖሩ እርሱ ግን እናንተን አላዋቂ አድርጎ የሐሰት ትምህርትን ያስተምራችኋል በማለት የሚናገሩትን ለማስተማር ጽፎላቸዋል።

5. ወደ ኤፌሶን ሰዎች

ኤፌሶን በሮሜ መንግስት ሥር በታናሺ እስያ በምዕራብ በኩል በከይስተር ወንዝ አጠገብ ወይም በኤጅያን ባሕር ዳር የምትገኝ የልድያ የወደብ ከተማ ነበረች።ዛሬ በቱርክ ውስጥ የምትገኝ ሀገር ናት።ቅዱስ ጳውሎስ በ 58 ዓ.ም በኢየሩሳሌም ተይዞ ወደ ሮም በመሄድ በቁም እሥር በነበረ ጊዜ የኤፌሶን ሰዎች በእምነት በምግባር መጽናታቸውን በመስማቱ ይህችን መልእክት በደቀመዝሙሩ በቲኪቆስ እጅ ላካቸው።ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ ታስሮ ሳለ ከጻፋቸው አራት መልእክታት የመጀመሪያይቱ ናት። አራቱም መልእክታት ወደ ኤፌሶን ወደ ፊልጵስዮስ ወደ ቆላስይና ወደ ፊልሞና ናቸው።

- ❖ ወደ ኤፌሶን ሰዎች የጻፈበት ምክንያት
- ✓ በልዩ ልዩ የዓለም ሰዎች ምቀኝነትና ተንኮል ኤፌሶንን ከለቀቀ በኃላ በክርስትያኖች ላይ የተለያየ ስም ሲያወጡባቸው ይሰማ ነበር።ይህን በክርስቶስ የተሰጣቸውን አዲስ ስም እርሱም ክርስቲያን መባልን ታላቅ እንደሆነ ለማስረዳት
- ✓ ከተማዋ ታላቅ እንደመሆኗ መጠን የዝሙት ኃጥያት በጣም ተስፋፍቶ ነበርና የዝሙትን አስከፊነት ገለጸላቸው
- ✓ ባልና ሚስት የማይከባበሩ የጋብቻውንም ምስጢር ያልተረዱ ስለነበር ስለ ቅዱስ ጋብቻ ታላቅነት በክርስቶስና በቤተክርስቲያን እየመሰለ ጻፈላቸው።ኤፌ **5÷32**
- ✓ አይሁድና አሕዛብ መለያየትን ያበዙ ስለነበር በክርስቶስ አንድ ስለመሆናቸው በግልጽ ጽፎላቸዋል።
- ✓ እንዲሁም የዲያብሎስን ተንኮል ባለማወቅ ተመልሰው ወደ ቀደም ግብራቸው እንዳይመለሱ የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ በመልበስ ዲያብሎስን ለመቃወም እንዲችሉ ጻፈላቸው። ኤፌ **6÷10-18**

6 ወደ ፊልጵስዮስ ሰዎች

ፊልጵስዮስ በቀድሞ ዘመን አሊኒደስ ትባል ነበር።የታላቁ እስክንድር አባት የመቄዶንያው ንጉስ ፊልጶስ ሁለተኛ ግዛቷን አስፋፍቶ በስሙ ፊልጵስዮስ ብሎ ሰይሟታል።በ 60 ዓ.ም በሮም ታስሮ የጻፋት መልእክት ስለ ክርስቶስ አምላክነትና ሰው መሆን የምታስረዳ የሃይማኖት ት/ት ናት።በተጨማሪም ክርስቶስ ከአብ ትክክል እንሆነ፣በመስቀልም መሞቱን ትንሳኤውን ዕርገቱን መጥቶም ይህም ዓለም እንዲያሳልፍ ያለውን የዳግም ምድአቱን ነገር ትናገራለች።

- ❖ መልእክቷ የተጻፈችበት ምክንያት
- ✓ ቅዱስ ጳውሎስ በሮም እስር ቤት በመሰቃይት ላይ መሆኑን የተረዱ የፊልጵስዮስ ምዕመናን ኦፍሮዲጡ በተባለ ወኪላቸው ያወጡትን አስትዋጽኦ አስይዘው ላኩት።እርሱም በመከራው የማይዘነጉት በሃይማኖታቸው ጽኑ መሆናቸውን የሚያበረታታ ምስጋናና ምክርና ትምህርት ጻፈላቸው። /ፊልጵ **4÷14-20/**
- ✓ ራሳቸውን ከፍ ከፍ ያደርጉ ይመኩም ስለነበር ለዚህ መልስ ጽፎላቸዋል።
- ✓ እርሱ መታሰሩን የስሙ ቢጽ ሐሳውያን እኛም መምህራን ነን እያሉ በፊልጵስዮስ ክርስትያኖች ላይ ችግር ፈጥረውባቸው ስለነበር ለዚህ መልስ ጽፎላቸዋል
- ✓ በተጨማሪም በከተማዋ የነበሩት አይሁድ እኛ የአብርሃም ዘር ነን እያሉ በአህዛብ ላይ ስለተመኩባቸው ከንቱ የሆነ ትምክህታቸውን እኔም እኮ የቢንያም ዘር ነኝ በማለት ለሁሉም መልስ በመስጥት ጽፎላቸዋል።

7. ወደ ቆላስይስ ሰዎች

የቆላስይስ መልእክት በ58 ዓ.ም አካባቢ ተጽፎ በቲኪቆስና አጥሲሞስ እጅ ተላከች።

- ❖ የተፃፈችበት ምክንያት
- ✓ ቢጽ ሐሳውያን የፍልስፍና መርዛቸውን እየረጩ መሆኑን ስለነገሩት ከዓለማውያን የቢጽ ሐሳውያን ፍልስፍና እንዲጠበቁ የእግዚአብሔር ማንነትና የጌታችን አዳኝነት በመግለጥ ጻፈላቸው።
- ✓ የፊልሞና አገልጋይ አንሲሞስ የቆላስይስን የኦሮ ሁኔት ሰለነገረው ስለክርስቲያናዊ ኦሮ ሁኔታ አብራርቶ ጽፎላቸዋል።

8. የመጀመሪያይቱ ወደ ተስሎንቄ ሰዎች

ተስሎንቄ ቀድሞ የመቄዶንያ ዋና ከተማ ስትሆን ዛሬ የግሪክ ሁለተኛ ከተማ ናት።የቀድሞ ስሟ ቴርማ ይባል ነበር ትጉሙም «ፍል ውሃ» ማለት ነው።አጠገባዋ ከነበረው ከፍል ውሃ የተወሰደ ይመስላል ቅዱስ ጳውሎስ ይህችን የመጀመሪያይቱን መልእክት የፃፋት በአቴና ውስጥ ነው ይህችንም መልእክት በ50 ዓ.ም አካባቢ ጽፎ በስልዋኖስ (በዕብራይስጥ ሲላስ በተባለው) እና በጢሞቴዎስ በደቀመዝሙሩ እጅ ተላከላቸው።

- ❖ መልእክቲቱ የተጻፈችበት ዐበይት ምክንያቶች
- ✓ ቀድሞ በብጥብጥ ምክንያት በድንገት ስለወጣ የተሰሎንቄ ክርስቲያኖችን ለማጽናናት ጠላት ሰይጣን እንዳይቃወማቸው የእርሱም ድካማ ከንቱ እንዳይሆን የመንፈስ ቅዱስ ልጁን ጢሞቴዎስን አስይዞ ላከላቸው
- ✓ ምንም እንኳን መከራና ስደት ቢበዛባቸውም ከሃይማኖት ያለ መናወጣቸው እርስ በርስም በፍቅር መኖራቸንነ ቅዱስ ጳውሎስንም ያልረሱ መሆኑን ሌሎችም አስደሳች ዜናዎች ነግሮት ስለነበር በዚህ ምክንያት ጻፈላቸው
- ✓ የተሰሎንቄ ምዕመናን ክርክርን ያበዙ ስለነበር የተማሩትን ትምህርትና ሃይማኖት መጠበቅ እንጂ መከራከር እንዳይዙ ጻፈላቸው።
- ✓ ሰው ሲሞትባቸው የቀቢጸ ተስፋን ነገር እያነሱ ከመጠን በላይ ያለቅሱ ያዝኑ ተስፋ ይቆርጡም ነበርና ይህን የአሕዛብ ሥራ ክርስትያን ሊሠራቸው እንዳማይገባ ጽፎላቸዋል።
- ✓ እርስ በእርሳቸው የተፈቃቀሩ እየመሰላቸው አንዱ ሚስቱን ለሌላው በመስጠት የማይገባ ሥራ ይስሩ ስለነበር ጽፎላቸዋል

በአጠቃላይ ፍፁማኑን የበለጠ ለማበረታት ተከፍሎ ልብ ያላቸውን ለማጽናት አንዳንዶችንም ለመገሰጽ ጽፎላቸዋል

9. ሁለተኛይቱ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች

በተሰሎንቄ የሚገኝ አይሁድ ራሱን ቅዱስ ጳውሎስን ሲያስጨንቁት እንደነበር የተሰሎንቄ ክርስቲያኖችም ያስጨንቋቸው ነበርና የሚያጽናና መልእክቱን በ51 ዓ.ም በጢሞቴዎስና በሲላስ እጅ ልኮላቸዋል።

- ❖ መልእክቲቱ የተጻፈችበት ምክንያት
- ✓ በነገረ ምጽአት ዙሪያ ብዙዎች መናፍቃን ያስቸገሯቸው ስለነበር በሰማ ጊዜ ይህችን መልእክት ጻፈላቸው
- ✓ የእርሱ መልእክት መሆኗን ስሙን በመጥቀስ እንዲቀበሉት አረጋግጦ ጽፎላቸዋል።

10. የመጀመሪያቱ ወደ ጢሞቴዎስ

ጢሞቴዎስ የቅዱስ ጳውሎስ (በሃይማኖትና በትምህርት የወለደው) የበኩር ልጁ ነው **1** ኛ ጢሞ **1÷2** ቅዱስ ጢሞቴዎስ በዕድሜ ወጣት ሲሆን በሃይማኖትና ምግባር የጸና መንፈሳዊ ቅናት ያለው ስለሆነ ቅዱስ ጳውሎስ ዲቁና ሰጠው ለቅዱስ ጳውሎስ የሥራ ረዳት የመከራ አጋር ሆኖት በሄደበት ሀገር አብሮ እየዞረ ሲቆይ በልዩ ልዩ ሀገሮችም ብዙ መልእክታትን ሳይደክም እየተላከ መንፈሳዊ ግዳጁን ፈጽሟል።በመጨረሻም ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስትያን ጳጳስ አድርጎ ሹሞታል።አንድ ጊዜ መታሰሩም ይናገራል ሐዋርያው ተልእኮውን እየፈጸመ እያለ በ96 ዓ.ም አካባቢ በሰማዕታትነት አርፏል።

- ❖ መልእክቲቱ የተጻፈችበት ምክንያት
- ✓ ከዚህ ቀድሞ ስለሥርዓተ ኖሎት ያልጻፈ ስለነበር በዚህ ምክንያት ጻፈለት
- ✓ በኤፌሶን ከተማና በአካባቢዋ ባሉት ሀገሮች የተስፋፋውን የግኖስቲኮችን ፍልስፍና አጠቃላይ ሁኔታ ክርስቲያናዊ ምላሽ በመሰጠት ጻፈለት
- ✓ ጢሞቴዎስን ለማበረታት ጽፎታል

11.ሁለተኛይቱ ወደ ጢሞቴዎስ

ይህች መልእክት ለሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሁለተኛው እሥራቱ በሮም ወኃኒ ቤት እያለ የጻፋት የመሰናበቻ መልእክቱ ናት።በዕድሜ የ 74 አመት አዛውንት ሲሆን በጨለማ እስር ቤት ከአንድ ዓመት በላይ በመኖሩ ዓይኖቹ ደክመው ጊዜ ሞቱም ደርሶ እንደነበር ታውቋል መልእክቲቱን በ 66 ዓ.ም ጽፎ በአንክሮሎስ እጅ ልኮታል።ቅዱስ ጳውሎስ መልእክቱን ከጻፈ ከ 1 ዓመት ከ 3 ወር በኃላ በሰማዕትነት አርፏል።

- ❖ መልእክቷ የተጻፈበት ምክንያት
- ✓ ለጢሞቴዎስ መሰነባበቻ መልእክት ጽፎለታል
- ✓ የመከረውን ምክር በድጋሚ ለማጽናት ጽፎለታል
- ✓ ከሐሰተኞች መምህራን ሕዝቡን እንዲጠብቅ ለማሳሰብና ለመሞከር

12.ወደ ቲቶ

ቲቶ በቅዱስ ጳውሎስ ስብከት ስላመነ በሃይማኖት የወለደው ልጁ ነው።ሐዋርያዊ ተልእኮውንና መንፈሳዊ ትጋቱን ተረድቶ ቅዱስ ጳውሎስ በሚድትራንያን ባሕር አጠገብ በምትገኝ ደሴት የቀርጤክስ ቤተ ክርስትያንን እንዲያስተዳድር በውስጧ አይሁድ ለሚኖሩባት ሀገር ሊቀጳጳስ አድርጎ ዲያቆናትንና ቀሳውስትን እንዲሾም እንዲያስተማር ሾሞታል።ቅዱስ ጳውሎስ መልእክቱን በ 63 ዓ.ም አካባቢ አርጣ በተባለው ደቀመዝሙር ጽፎታል።

- ❖ መልእክቷ የተጻፈችበት ምክንያት
- ✓ የቀርጤክስ አብያተ ክርስቲያናት በልዩ ልዩ ቦታዎች ተቋቁመው በቁጥር በዝተው ቢገኙም በጣም ያልተደራጁ የወንጌል አገልግሎትም በአንዳንድ ቦታዎች ያልተዳረሰ መሆኑን ተረድቶ ነበር ወንጌል እንዲያስፋፉባቸው በአስተዳደርም በኩል መመሪያ በመስጠት ይህችን መልእክት ጻፈለት።
- ✓ የቀርጤክስ ሰዎች ጠባያቸው የከፋ ስማቸው የጠፋ ነበርና መከራ እንዳይበዛበት መከራ ቢመጣበትም እንዲታገስ አስቀድሞ የሰዎቹን ጠባይ በማስገንዘብ አገልግሎቱም እንዳይጎዳ ጽፎታል።
- ✓ በሀገሪቱ ብዙ ዓለማውያን ሰዎችና መናፍቃን ስለነበሩ ከእነርሱ እንዲርቅ ምእመናኑም ግንኙነት እንዳይኖራቸው በክፉ ትምህርታቸው እንዳይሳቡ ክህደታቸውን እየገለጠ ጽፎለታል።
- ✓ በመጨረሻም በትምህርትና በግብረ ገብነት የታወቁትን በመምረጥ የቤተ ክርስትያን ጠባቂ የሚሆኑትን እንዲሾም እርሱም በትጋት እንዲያገለግልና እንዲጸና ይህችን መልእክት ጽፎለታል።

13.ወደ ፊልሞና

ሀገሩ ቆላስዮስ የሆነው ፊልሞና ደግ ባለጸጋ ሲሆን ወደ ኤፌሶን ለሥራ በሄደ ጊዜ የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስን ስብከት ሰምቶ ከእነቤተሰቡ አምኖ ተጠምቋል።ይህ ሰው አብርሃማዊ ሕይወት የነበረው ክርስትያኖችን በቤቱ እየተቀበለ ያበላ ያጠጣና ያሳድርም ነበር ቅዱስ ጳውሎስንም ይንከባከበው ለአገልግሎቱም የሚያስፈልገውን ያደርግ ነበር ከኤፌሶን ወደ ቆላስይስ ተመልሶ አናሲሞስ የተባለ አገልጋይ ነበረው ይህ አገልጋይ የሚጠበቃቸው የፊልሞና ኩበቶች ሲጠፉበት አገሩን

ቆላስይስን ትቶ ወደ ሮሜ ሲገባ ቅዱስ ጳውሎስ በመጀመሪያ እስራቱ ላይ ሳለ አናሲሞስ የቅዱስ ጳውሎስን ትምህርት ሰምቶ አምኖ ተጠመቀ።ወደ ሮሜ ለምን እንደመጣም የደረሰበትን ሁኔታ ሲነግረው ይህች የማስታረቂያ መልእክት ለፊልሞናና ለሚስቱ ለአፋብያ እንዲሁም ለልጁ ለአክርጳስ ጽፎ በአናሲሞስ እጅ በ60 ዓ.ም አካባቢ ላከላቸው።

❖ *መልእክቷን የጻፈበት ምክንያት*

- ✓ አናሲሞስ ከፊልሞና ተጣልቶ በስደት ወደ ሮሜ እንዳይቀር ይህችን መልእክት አሲዞ ላከው።
- ✓ ፊልሞናና አፋብያ በአናሲሞስ መጥፋት እንዳያዝኑ መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን ከመወጣት ወደ ኋላ እናዳይሉ ከበቶችን መጠበቅ ብቻ ሳይሆን የተጠመቁ ክርስትያን ወገኖችን ሁሉ እያስተማረ ከእነርሱ ጋር ሆኖ ያበረታቸው ዘንድ መልእክቱን በእጁ አስይዞ ልኮላቸዋል።
- ✓ ስለጠፋው የፊልሞና ንብረትና በዚህ ምክንያት በክርስቲያኖች መካከል ልዩነት እንዳይኖር አጠቃላይ ሁኔታ ጽፎለታል።

14.ወደ ዕብራውያን ሰዎች

ዕብራውያን(ከአብርሃም ቅድመ አያት) በአባታቸው በዔቦር ዕብራውያን የተባሉ በኢየሩሳሌም ያሉ ምዕመናን እና አይሁድ ናቸው።ይህ ስም በሐዲስ ኪዳን ዘርን ወይም ዜግነትን ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ሕግ በመጠበቅ ስለሚገኝ ጽድቅ የሚያስረዳ ነው።

ይህች መልእክት የተጻፈችው ሮማውያን የኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ ካፈረሱበት ከ70 ዓመት በፊት ነው።መልእክቷም የሙሴን ሕግ፣የቤተመቅደሱን አገልግሎት የነገስታቱንና የመሳፍንቱን ታሪክ ትውፊትና ሥርዓት ጠንቅቀው የሚያውቁ አይሁዶች በሚበዙባቸው ሀገሮች በኢየሩስአሌም በኢጣሊያና በእስክንድሪያ ለሚኖሩ ክርስቲያኖች (ከአይሁድነት ወደ ክርስትና ለተመለሱ) የተጻፈች ናት።

የዚህች መልእክት ፀሐፊ ማነው? የሚለው ጥያቄ ለሔሬኔዎስ ለሂፖሊተስ ለጠርጡለስና የማርቲን ሉተርን ሀሳብ መሰረት ላደረጉ ለብዙዎች ነገረ መለኮት ምሁራን አጠያያቂ ሆኖ ቆይቷል። ብዙዎች ይህ መልእክት የቅዱስ ጳውሎስ አይደለም ለማለት የሚገልጿቸው ምክንያቶች፡-

- ✓ አጻጻፉ ከቅዱስ ጳውሎስ የአጻጻፍ ባሕርይ የተለየ ነው
- ✓ መልእክቱ የተላከው ለዕብራውያን እንደመሆኑ መዘጋጀት የነበረበት በዕብራይስጥ ቋንቋ ነበር ነገር ግን መልእክቱ የተዘጋጀው በግሪክ ቋንቋ ነው
- ✓ በመልእክቱ መጀመሪያ ላይ በሌሎች መልእክቶች የተለመደውን የሰላምታ አሰጣጥ አልተጠቀመም
- ✓ የእርሱ ቢሆን ስሙን ሊገልጽ ይችል ነበር…የሚሉ ናቸው።

ከ185-240 ዓ.ም የነበረው አርጌንስ ከ150-215 ዓ.ም የነበረው ቀሌምንጦስ ዘእስክንድሪያ ዮሐንስ አፈወርቅ ቅዱስ አትናቲዮስና ሌሎችም የቤተ ክርስትያንን ትውፊት መሠረት በማድረግ ቅዱስ ጳውሎስ እንደጸፈው ተናግረዋል።ታላቁ የቤተ ክርስትያን ታሪክ ፀሐፊ ቅዱስ አውሳብዮስም በ340 ዓ.ም የዕብራውያን መልእክትን ከቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ዝርዝር ውስጥ አካቶታል።በ397 ዓ.ም በቅርጠግና(chartage) ላይ የተደረገ የቤተ ክርስትያን ጉባኤም የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት በቀኖና ደንግጎ አስቀምጦታል።

እነዚህ የቤተ ክርስትያን ሊቃውንት መልእክቱ የቅዱስ ጳውሎስ ነው ሲሉ በመረጃና ከላይ ያልቀበሉትን ሰዎች ጥያቄ መልስ እንደሚከተለው በመስጠት ነው።

- ✓ የአጻጻፉ ባሕሪ የተለየው ቅዱስ ጳውሎስ ጥልቅ የኦሪት እውቀት ስላለው መልእክቱ ተቀባይነት እንዲኖረው ከሌሎቹ መልእክታት ለየት አድርጎታል።

- ✓ ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራይስጥ ቋንቋ ከጻፈው በሃላ ወደ ግሪክ ቋንቋ የተረጎመው ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ነው።
- ✓ ቅዱስ ጳውሎስ ከሌሎቹ መልእክቶቹ ሁሉ በእርሱ እንደተጻፈ ማረጋገጫ አድርጎ የተናገረው የሰላምታ ቃል በዚሁ መልእክትም ተገላጽዋል።ዕብ 13÷25
- ✓ ጥልቅ ዕውቀት ያለው ለአጻጻፍና ለአቀራረቡ ምንም አይነት ችግር የሌለበት ቅዱስ ጳውሎስ የዕብራውያን ሰዎች ከእግዚአብሔር ተለይተው እንዳይቀሩ ሕጉን ሥርዓቱንና ትውፊቱን እንዲጠብቁ በሚገባቸው ኦሪታዊ አገላለጽ እንዲመልሱ ለማድረግ የጻፈላቸው በመሆኑ ነው።
- ✓ ስሙን በመልእክቱ ውስጥ ያልገለጸበት ምክንያት፡-
  - አስቀድሞ የእርሱ ተማሪና ለወጋቸው ቀናተኛ ስለነበር ስሙን ቢያዩ ኖሮ ለበቀል ስሜት መልእክቱን ስለማይቀበሉት ነው።
  - ዘመኑ አይሁድ በሮማውያን ላይ ለማመጽ የተዘጋጁበት ጊዜ ስለነበር በሮም መንግስት የቁም እስረኛ ላይ በመሆኑ በግዞትና በጦርነት ጊዜ መተማመን ስለማይኖር ሮማውያን ካወቁ ወገኖቹን ያነሳሱብናል ብለው እንዳይቃወሙትና ምክንያት አግኝተው እስራቱን ወደ ፖለቲካ እንዳያዞሩበት።
  - ቀድሞውንም ያሳሰሩት እነርሱ ናቸውና ገና ስሙን ሲያዩ ኦሪት አለፈች ሊለን ይሆናል ብለው ከማንቡብ እንዳይከለከሉ፣ነጻ ሆነው መልእክቱን አንብበው ወደ ክርስትና ያልመጡትን ለማምጣት የመጡትን ደግሞ ለማጽናት ጽፎላቸዋል።
- ✓ በመጨረሻም «ወንድማችን ጢሞቴዎስ እንዲፈታ ዕወቁ» ከኢጣልያ የሆኑት ሰላምታ ያቀርቡላቸዋል። ዕብ **13÷23፣13÷24** የሚሉት መረጃዎች ፀሐፊው ከጢሞቴዎስ ጋር ያለውን ቅርብ ግንኙነትና በኢጣልያ በአገልግሎት እያለ የጻፈው መሆኑን ያስረዳል በማለት መሠረታውያን የቤተ ክርስትያን አባቶች በእነዚህና በመሳሰሉት መረጃዎች መስክረዋል። ይህች መልእክት በመጀመሪያዋ እስራቱ በሮሜ እያለ በ 60 ዓ.ም አካባቢ ጽፎ በጢሞቴዎስ እጅ ልኮላቸዋል።

❖ *መልእክቲቱ የተጻፈችበት ምክንያት*

- ✓ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር መምጣት እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውሃ ፈሳሽ አለመሆኑን ለማስረዳት
- ✓ ኢየሱስ ክርስቶስ ከነቢያት ከመላእክት እንዲሁም በክህነቱ በመሥዋዕቱ በሕጉ በኪዳኑ በሚያወርሰን መካነ ዕረፍት ወ.ዘ.ተ... የሚበልጥ መሆኑን ለማስረዳት
- ✓ በወቅቱ ክርስትና በተቀበሉ ግሪክኛ ተናጋሪ በነበሩ አይሁድ ላይ ስደትና መከራ ስለጸናባቸው በእምነታቸው ጸንተው መከራውን ታግሰው የጽድቅ አክሊል ተካፋዮች እንዲሆኑ ለመምከርና ለማጽናት
- ✓ በኦሪት ሕግ ብቻ ይኖሩ የነበሩ ወደ ክርስትና ሃይማኖት ያልተመለሱ ብዙ አይሁዳውያን መልእክቱን አንብበው ይመልሱ ዘንድ ጽፎላቸዋል።

❖ *ሰባቱ መልእክታት*

የቅዱስ ጴጥሮስ 1 ኛ እና 2 ኛ፤ የያዕቆብ የዮሐንስ 1 2 እና 3 የይሁዳ እነዚህ ሰባቱ መልእክታት በመባል ይታወቃሉ። እነዚህም ሰባቱ መልእክታት የተባሉበትም ምክንያት ለአንድ ሰው ወይም ለአንድ ቤተ ክርስትያን ብቻ ስላልተጻፉ ማለትም ለአብያተ ክርስትያናት ስብስቦች የተላኩ መልእክታት መሆናቸው ነው።

መልእክታቱም ሲላኩ ከአንድ ቤተ ክርስትያን ይደርስና ለምእመናኑ ከተነበበና ከተረዱ በኋላ ሀብት ያላቸው አጽፈው ቅጅ ያስቀሩና ዋናውን ላዋሳቸው ወይም ለሌላ ቤተ ክርስትያን እንዲደርስ በማሰብ ያስተላልፉና ይጠቀሙበት ነበር።

.የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክታት

1. *የመጀመሪያይቱ የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት*

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ የመጀመሪያይቱን መልእክት የጻፈው በመከራና በስደት ጊዜ ነው።መልእክቷ የተጻፈችው በቅዱስ ጴጥሮስ ነጋሪነት በስልዋኖስ እጅ ሮም (ባቢሎን) ውስጥ በ 60 ዓ.ም አካባቢ እንደሆነ ይነገራል።

- ❖ መልእክቷ የተጻፈችበት ምክንያት
- ✓ መልእክቱ ያለምንም ምክንያት ሊደርስ ከሚችል ፈተናና ችግር ጌታችን እንደታገሰ እንዲታገሱ ለመምከር
- ✓ በንጹህ ደም የተዋጁ ስለሆኑ በንጽህና እንዲኖሩ በክርስቶስ ላይ እንደተመሰረቱ ካህናትና ቤተመቅደስ እግዚአብሔርን እንዲያገለግሉ
- ✓ የዘለአለም ህይወት እንዳላቸው ያውቁ ዘንድ
- ✓ ከሥጋ ምኞት እንዲጠበቁ
- ✓ ከምእመናን ሁሉ ጋር ባላቸው የሚገባ ግንኙነት ትሁታን እንዲሆኑ ጽፎላቸዋል።

2. ሁለተኛይቱ የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት

ይህች መልእክት በቅዱስ ጴጥሮስ ተጽፋለች።የጻፈላቸውም በኒሮን አዋጅ ተይዞ በእሥራት እያለ በ 67 ዓ.ም አካባቢ ነው።

- ❖ መልእክቲቱ የተጻፈችበት ምክንያት
- ✓ ሐሰተኞች ነቢያትና ሐሰተኞች መምህራን
- ለዚህ ዓለም ሠራኢ መጋቢ የለውም
- ትንሣኤ ሙታን የለውም
- ጎልፈተ ሰማይ ወምድር የሌም
- አንድ ጊዜ ካመኑ ምግባር አይጠቅምም እያሉ በክህደት ትምህርታቸው ያላመኑትን ምግባር ያላቸውን ክርስትያኖች ያውኳቸው ስለነበር ለእነዚህ ሰዎችና ለጥያቄዎቻቸው መልስ በመስጣት ይህን መልእክት ጽፎላቸዋል።
- ✓ የሚገባውን የክርስትያን እኗኗር ሕይወትና መሠረቱ የቤተ ክርስትያን መሥራች የቅዱሳን ሁሉ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ያወቁና በክርስትና እምነት ይጸኑ ዘንድ ጽፎላቸዋል።
- ✓ ያመኑት ሰዎች ይህን መልእክት ተረድተው በሃይማኖት በምግባር እንዲኖሩ ሌሎች ምግባር ሃይማኖት የሌላቸው አንብበው ተረድተው ይመለሱ ዘንድ ይህን መልእክት ጽፏል።

3. የመጀመሪያው የቅዱስ ዮሐንስ መልእክት

ቅዱስ ዮሐንስ በኤፌሶን ሳለ በ 96 ዓ.ም አካባቢ እንደጻፈው ይገራል።

- ❖ መልእክቷ የተጻፈችበት ምክንያት
- ✓ መናፍቃን
- ትንሳኤ ሙታን የለም
- ከጥምቀት በኋላ የምንሰራው ኃጢአት አይደለም ከዚህ የተለየ ምግባርም አያስፈልግም
- ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ አልተገለጠም
- (ግኖስቲኮች) (አዋቂዎች) ነን በማለት ያለ እነርሱ እውነተኛ ክርስትያን እንደሌለ በማሰብ ለእኛ የመጨረሻ እውቀት ተገልጦልናል።ስለዚህ ያለ ሕግ መኖር እንችላለን የሚሉትን የተለያዩ ጥያቄዎቻቸውን አንድ በአንድ በመመለስና በማስረዳት ጽፎላቸዋል።

ይኸውም

1. ስለትንሣኤ ሙታን መኖርና የጌታችንን መለኮታዊ ክብርና ምሥጢረ ስጋዌውን በማረጋገጥ

2. ማንኛውም ክርስትያን የእግዚአብሔርን ትእዛዛት መጠበቅ እንዳለበትና ድኅነት የሚገኘውም ለእርሱ አምልኮ በማቀረብ እንደሆነ

3. ክርስቶስ የሰውን ልጅ ስለመውደዱና እርስ በርስ መዋደድ ዓይነተኛ የክርስትና ምልክት እንደሆነ

4. ኃጥያቱን የተናዘዘ የእግዚአብሔርን ምህረት የሚያገኝ እንደሆነ

5. የሐዋርያት ትምህርት አጽንተው መያዝ ያለባቸው ስለመሆኑ

6. ስለ እውቀት ምንነት አጠቃላይ ሁኖታ አስረድቶ ከፍጥሞ ደሴት ግዞቱ ሲወጣ ለመናፍቃን የክህደት ትምህርት መልስ ይሆን ዘንድ ጽፎላቸዋል።

4.ሁለተኛይቱ የቅዱስ ዮሐንስ መልእክት

ይህች መልእክት ሐዋርያው ዮሐንስን በኤፌሶን ከተማ በ96 ዓ.ም አካባቢ ለአንዲት ሴትና ቤተሰቧቿ ከመናፍቃን ትምህርት እንድትጠበቅ የጻፈላት መልእክት ነው።

ይህች ሴት በኤጅያን ደሴቶች አንዱ ቀለብ እየተሰፈረላት የነገስታቱን ልጆች የምታሳድግ ሮምና የተባለች ሞግዚት ነበረች ዮሐንስና ደቀመዝሙሩ አብሮኮሮስ በዚህች ደሴት ለማስተማር ፈልገው «የሮምና የአባቷ ባሮች ነበርን ለብዙ ዘመናት ጠፍተን ስንኖር አሁን መጣን» እያሉ በደሴቷ አስወሩ።ከንቱ ውዳሴ የሚያጠቃት ሴት ነበረችና ወደ ቤቷ ወስዳ ቅዱስ ዮሐንስን እንጨት ፈላጭ ደቀመዝሙሩ አብሮኮሮስን ደግሞ ውሃ ቀጅ አደረገቻቸው።

አንድ ቀን ከምታሳድጋው አንዱን ይዛ ወደ ቤተ ጣዖት ስትገባ ዮሐንስና አብሮኮሮስ ተከትለዋት ገቡ።ያን ጊዜ በቤተ ጣዖቱ ያደረው ሰይጣን እነ ቅዱስ ዮሐንስን ሲያይ የቤቱን እቃ በማተረማመስ ወጣ።በዚህ መካከል አስከትላው የነበረው ልጅ በድንጋጤ ሞተ ያን ጊዜ «የእናንተ መምጣት ነው ለዚህ ሁሉ ያበቃኝ» ብላ ደበደበቻቸው ቅዱስ ዮሐንስም «አስነሱልኛ አትይምን?›› ሲል መለሰላት «ያሁኑ ይባስ!ከመቼ ወዲህ ነው ደግሞ የሞተ ሰው የሚነሳው ብላ የበለጠ ተቆጣች» ያን ጊዜ እነ ቅዱስ ዮሐንስ ጸልየው አስነሱላት።በዚህ ተአምር ምክንያት በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምና ተጠምቃለች። ወድያውኑም በቤቷ የምእመናን ጉባኤ ተጀምሮ እርሷንም ለዚህ እመ መኔት አድርገው ሾመዋታል።ቅዱስ ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት በታሰረ ጊዜ በመናፍቃን የሐሰት ትምህርት የተነሳ በቤቷ ያለው የክርስቲያኖች ጉባኤ መከፋፈል ደረሰበት ጠበ ክርክር ተነሳ ይህን የሰማው ቅዱስ ዮሐንስም የድሮ ኑሮዋን ወይም ህይወቷን አስታውሳ የአሁኑን መከራ እንድትረሳ እመመኔትነቷም ለትእቢት እንዳይሆንባት ታላቁ ሐዋርያ በድሮ ስሟ «እመቤቴ» እያለ በትህትና በመጥራት አጠቃላይ ሁኔታውን ጽፎላታል።

- ❖ መልእክቲቱ የተጻፈችበት ምክንያት
- ✓ በመጀመሪያቱ የዮሐንስ መልእክት ላይ የተገለጹት መናፍቃን ምእመናንን ለማስካድ ይጣደፉ ስለነበር የሐስት ትምህርታቸውን በመቃወም እውነተኛዋን የክርስትና ትምህርት እንዲያጸኑ ነው።

5.ሶስተኛይቱ የዮሐንስ መልእክት

መልእክቱ የተላከችው ጋይዮስ ለተባለ ሰው ነው።በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ጋይዮስ በመባል የሚጣወቁ 3 ሰዎች ሲኖሩ ይህችን መልእክት ለማድረስ የታደለው በሮሜ **16÷23** ለተጠቀሰውና በአብርሃማዊ እንግዳ አቀባበል በረከት ለደረሰው ጋይዮስ ነው።

- ❖ መልእክቱን የጻፈበት ምክንያት
- ✓ ጉባኤው ይሰፋ ዘንድ እንግዳ እየተቀበለ የሚያገለግለውን ጋይዮስን ለማመመስገን
- ✓ በቤተክርስትያን ውስጥ መለያየት እንዳይኖር ለመምከር
- ✓ ዲዮጥራጢስን ለመገሰጽ ፅፏል

6.የሐዋርያው የቅዱስ ያዕቆብ መልእክት

በሐዲስ ኪዳን ያዕቆብ በመባል የሚጠሩ ቅዱሳን አባቶች አሉ።

- ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ (የዮሐንስ ወንድምና ከሚስጥር ሐዋርያ አንዱ)
- የይሁዳ(ሐዋርያው) አባት ይህም ታዴዎስ ወይም ልብድዮስ እየተባለ የሚጠራው
- የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስትያን መሪ የጌታ ወንድም የተባለውና ይህን መልእክት የጻፈው ነው።

❖ መልእክቱ የተጻፈበት ምክንያት

✓ መልእክቱ የተላከላቸው ሰዎች (ተበትነው ይኖሩ ለነበሩና ክርስትናን ለተቀበሉ አይሁድ) ተበታትነው ስለነበር በያሉበት ለማበረታታትና ለማጽናናት

✓ ስደትና መከራ ይበዛባቸው ስለነበር በደረሰባቸው መከራና ስደት ተስፋ እንዳይቆርጡና ዋጋ እንደሚያገኙ እንዲሁም ክብር እንዳለው ለመምከር

✓ በቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት የተጻፈውን የነገረ ሃይማኖት ትምህርት እንዲያጸኑና በተጨማሪም ደግሞ ምግባር በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ለማስረዳት

7.የሐዋርያው ቅዱስ ይሁዳ መልእክት

በሐዲስ ኪዳን ውስጥ የይሁዳ ተብለው የሚጠሩ ብዙ ሰዎች አሉ።የዚህ መልእክት ጸሐፊ የጌታ ወንድሞች ከተባሉት አንዱ ነው።የያዕቆብን መልእክት የጻፈው የያዕቆብ ወንድም የተባለው የዮሱፍ ልጅ ሐዋርያው ቅዱስ ይሁዳ ነው።ሁለቱም ወንድማማቾች ከጌታ ትንሣኤ በኃላ ያመኑና የሰበኩ ናቸው።

❖ መልእክቱ የተጻፈበት ምክንያት

✓ በሐሰተኞች መምህራን ትምህርት ችግር የደረሰባቸው ክርስቲያኖች ከክህደት ትምህርት ርቀው ከቅዱሳን ሐዋርያት የተረከቡትን የቀና የክርስትና እምነት አጽንተው እንዲይዙ ለማድረግ

✓ ተመክረው ያልሰሙ ሰዎች እንደሚቀጡ የሚመለሱት ደግሞ እንደሚድኑ ለማሳወቅ ተጽፏል።

የቅዱስ ዮሐንስ ራእይ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመልአኩ አማካኝነት በራዕይ በገለጸለት መሠረት የዚህ መጽሐፍ ፀሐፊ ወንጌላዊው ዮሐንስ ነው።ዮሐንስ ለቁሳር ድምጥያኖስ ሐውልት የሚሰግዱትን በመቃወም በንጉሱ ትእዛዝ ወደ ፍጥሞ ደሴት ተጓዘ።

የቅዱስ ዮሐንስ ራእይ በግሪክ ቋንቋ «አቡቀለምሲስ» በመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ዘንድ ደግሞ «የሐዲስ ኪዳን የትንቢት መጽሐፍ» በመባል ይታወቃል።ፍፁምነትን ለመግለጽ በሰባቱ የእስያ አውራጃ ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ቢልም ለሁሉም አብያተ ክርስቲያናት የተላከ መጽሐፍ መሆኑ ይታመናል።የዮሐንስ ራእይ የትንቢት መጽሐፍ ሲሆን ከስነ ጽሑፍ ሁኔታ አንጻር በአጠቃላይ ሦስት አይነት አቀራረብ አለው።

✓ የጽሑፉ መግቢያና መደምደሚያ በማሳሰቢያ መልክ የቀረበ ነው

✓ በተለይ ምዕራፍ ሁለትና ሦስት ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት አለቃዎች የተላኩና በደብዳቤ መልኩ የቀረቡ ናቸው።

✓ ሌላው አብዛኛው ክፍል በራዕይ መልክ የቀረበ ሲሆን በብሉይ ኪዳን የመቅደስ ሥርዓትና ንዋየ ቅድሳት ወ.ዘ.ተ ምሳሌነት ለዮሐንስ የታየ ነው።

❖ ቅዱስ ዮሐንስ ራዕዩን የጻፈበት ምክንያት

✓ ብዙዎች የፋርስ ነገስታት የሰሩት የአርጤምስ ጣዖት በማምለካቸው ሁሉንም ሊያስተምር

✓ መላእክት(አለቃዎች) ተብለው ለተጠሩ በታናሿ እስያ ለሾማቸው ሰባት ሊቃነ ጳጳሳት በቤተ ክርስትያን መልካም አስተዳደርና ሕይወት ዙሪያ ለመምከር

- ✓ የክርስቲያኖችን ሰማያዊ ሕይወትና የመላእክትን የጻድቃንን የሰማዕታትን ክብር ለማሳየት ጽፏል።
- ✓ የጥሞስን የሐሳዊ መሲህን የምጽአትንና የመንግስተ ሰማያትን ነገር የገለጸለት እግዚአብሔር ጸፍ ብሎት ለማስረዳት ጽፏል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ወለወላዲቱ ድንግል

ወለመስቀሉ ክቡር!!!